# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ 81ኛ ዓመት ቁጥር 236 ሚያዝያ 26 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ


# ለዜጎች ስጋትን በሚፈጥሩ አካላት ላይ መንግሥት መውሰድ የጀመረውን እርምጃ አጠናክሮ ይቀጥላል

*-የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት*

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡-ለዜጎች በሰላም መኖር ስጋትን የሚፈጥሩ፤ በሃገር ሕልውና ላይም አደጋን የሚደቅኑ አካላት ላይ መንግሥት መውሰድ የጀመረውንም እርምጃ በተጠናከረ ሁኔታ እንደሚቀጥል የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ፡፡

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ወቅታዊ ጉዳይ ላይ ትናንት በሰጠው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ ከሰሞኑ በሃይማኖት ሽፋን በተለያዩ አካባቢዎች የተከሰቱ ሁከቶችና ወንጀሎች ላይ የተሳተፉ ተጠርጣሪዎችን የፌደራል ፖሊስ፣ የክልልና የከተማ አስተዳደር የጸጥታ ኃይሎች በቁጥጥር ስር እያዋሉ ይገኛሉ፡፡ ተጠርጣሪዎቹም ተገቢውን ፍርድ እንዲያገኙ ይደረጋል።

ለዜጎች በሰላም መኖር ስጋትን የሚፈጥሩ፤ በሃገር ሕልውና ላይም አደጋን የሚደቅኑ አካላት ላይ መንግሥት መውሰድ የጀመረውንም እርምጃ በተጠናከረ ሁኔታ እንደሚቀጥል በመግለጫው አስታውቋል፡፡

ባሳለፍነው ሳምንት ውስጥ ሃገራችን በርከት ያሉ ሃይማኖታዊና ባህላዊ በዓላትንና ሁነቶችን አስተናግዳለች

ለዜጎች ስጋትን በሚፈጥሩ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service






# የኢትዮጵያ አንድነትና ሰላም እንዲጠበቅ ተቋማት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪ ቀረበ



ፎቶ፦ ገባቦ ገብሬ

ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ አንድነትና የሕዝብ ሰላም አደጋ ላይ እንዳይወድቅ ክርስቲያንም ሙስሊምም የሃይማኖት አባቶች እና ሰላም ሚኒስቴር ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባ የታሪክ ተመራማሪና ጸሐፊ ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል ገለጹ፡፡

ረዳት ፕሮፌሰር አደም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሕዝብ አንድነትና የኢትዮጵያ ሰላም አደጋ ላይ እንዳይወድቅ ክርስቲያንም ሙስሊምም የሃይማኖት መሪዎች እና ሰላም ሚኒስቴር ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

የሕዝብ አንድነትና የአገር ሰላም እንዲጠበቅ የአገር መከላከያ ሠራዊትን ማጠናከር ይገባል ያሉት ረዳት ፕሮፌሰር አደም፤ የሃይማኖት መሪዎችና ሰላም ሚኒስቴር የተሰጣቸውን ሰላምና የሕዝብን ደህንነት ማስጠበቅ ካልቻሉ የአገር ደህንነት አደጋ ላይ ይወድቃል፡፡ በሰላም ወጥቶ መግባትም ያስቸግራል ብለዋል፡፡

ቀሳውስትም ሆኑ ሼኮች ከቤተ ክህነትና ከመስኪድ ወጥተው ወደ ሕዝቡ በመግባት የሕዝብ አንድነትን ማስተማር አለባቸው፡፡ አደጋውን ማሳየት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ኅብረትና አንድነት እንዲኖር በቀዳሚነት በመታገል እና በማስተማር ኃላፊነታቸውን መወጣትም ይገባቸዋል፡፡

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ኢትዮጵያ ኢስላምና ክርስቲያን ተቻችለው የኖሩባት አገር ናት፡፡ ሁሉም ሃይማኖቶች የሚሰብኩት ሰላምን እንደመሆኑ ክርስቲያኑም ሙስሊሙም ከእምነታቸው አንጻር ካስተማሩ ፈጣሪን የሚፈራ፣ ሕዝብን የሚያከብር

የኢትዮጵያ አንድነትና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








ፎቶ፡- ሐዲስ አብርሃ

የትግራይ ዴሞክራሲዊ ፓርቲ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ሙሉብርሃን ኃይሌ

## ሕወሓት እያደረሰ ያለው መከራ እንዲያበቃ የትግራይ ልሂቃን ድምጻቸውን እንዲያሰሙ ትዴፓ ጠየቀ

ገጽ 4

## በረመዳን ወቅት የታየ መልካም ተግባራትን ማስቀጠል እንደሚገባ ተገለፀ

ገጽ 3

## የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አገልግሎት መሻሻል እንዳለበት ተጠቆመ

ገጽ 4




# ‹‹የንፁሕ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ችግር የእለት ተእለት ኑሯችን ላይ ጫና ፈጥሯል››

## “የኮዬ ፈጬ የጋራ መኖሪያ ቤት ነዋሪዎች

## ‹‹ለአቅርቦት ችግሩ ጊዜያዊ መፍትሔ በማበጀት እጥረቱን ለመፍታት ተሞክሯል››

- የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን



ፎቶ አዮብ ተፈራ

**ፍቃዱ ዴረሳ**

አዲስ አበባ፡- የኮዬ ፈጬ የጋራ መኖሪያ ቤት ነዋሪዎች የንፁሕ መጠጥ ውሃ አቅርቦት እጥረት በኑሯቸው ላይ ጫና መፍጠሩን ገለፁ። ለአቅርቦት ችግሩ ጊዜያዊ መፍትሄ በማበጀት እጥረቱን ለመፍታት መሞከሩን የአዲስ አበባ ውሀና ፍሳሽ ባለስልጣን ገልጿል።

ነዋሪዎቹ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ችግር በመኖሩ የእለት ተእለት ኑሯችን ላይ ጫና ፈጥሯል። ለከፍተኛ ወጪም ዳርጎናል።

በኮዬ አንድ የጋራ መኖሪያ ቤት ነዋሪዋ ነፍሰጡርና የአንድ ልጅ እናት የሆኑት ወይዘሮ ፋጡማ አሕመድ በውሃ አቅርቦት ችግር ምክንያት ለንፅሕናም ሆነ ለምግብ ማብሰያ እንደሚቸገሩ ተናግረዋል። መንግሥት ከሚቀርበው የታንከር ውሃ በመቅዳት ወደ ጋራ መኖሪያ ቤት ለማጓጓዝ እንደሚቸገሩም ገልጸዋል።

በአካባቢው የውሃ ችግር በመኖሩ ምክንያት ከሌላ ቦታ በጋሪ በመቅዳት እስከ ሰባተኛ ፎቅ ለማጓጓዝ በአንድ የ20 ሊትር በሚይዝ የውሃ መቅጃ ከ25 እስከ 30 ብር በሥራው ላይ የተሰማሩ ወጣቶች ገልፀዋል።

በኮዬ ሁለት የሚኖሩ ነዋሪዎች በበኩላቸው፤ የውሃ አቅርቦት እጥረት በመኖሩ ምክንያት ውሃ የሚያገኙት በፈረቃ መሆኑንና ይህም የእለት ተእለት ኑሯቸውና ሥራቸው ላይ ጫና እንዳሳደረባቸው ተናግረዋል። በተለይም በንግድ ሥራ ላይ ከተሰማሩ ነዋሪዎች መካከል ወጣት ጥጋቡ ባጪሶ ‹‹በውሃ እጥረት ምክንያት ለመሥራት ያሰብነው ሥራ ላይ እንዳንሠማራ ሆነናል›› ብሏል።

ዝግጅት ክፍሉ ባደረገው ቅኝት ችግሩ እንደሚስተዋል አረጋግጧል። በተለይም ኮዬ አንድ ተብሎ በሚጠራው የጋራ መኖሪያ ቤት የመጠጥ ውሃ የማይደርስ መሆኑን እና በውሃ ጫኝ ተሽከርካሪዎች በመታገዝ ለነዋሪው ውሀ እየቀረበ መሆኑን ታዝቧል።

በአንፃሩ በተለምዶ ኮዬ ሁለት ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የውሃ አገልግሎት መኖሩን፣ ነገር ግን ይህ አካባቢም በፈረቃ በየሶስት ቀን ልዩነት እንደሚያገኝ ነዋሪዎችን ባነጋገረበት ወቅት ለመረዳት ተችሏል።

የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን በበኩሉ በኮዬ ፈጬ የጋራ መኖሪያ ቤት የሚስተዋለው የንፁሕ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ችግርን ለመፍታት እየሠራ መሆኑን አስታውቋል። በኮዬ አንድ የውሃ አቅርቦት አገልግሎት ባልጀመረባቸው አካባቢዎች በውሃ ጫኝ ተሽከርካሪ በቋሚነት እንዲቀርብላቸው መደረጉን አስታውቋል።

የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ምክትል ሥራ አስኪያጅ አቶ ፍቃዱ ዘለቀ እንደገለፁት ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከመንገድ፣ ከኤሌክትሪክ፣ ከኢትዮ ቴሌኮም እንዲሁም ቤቶች ልማት መሥሪያ ቤቶች ጋር የጋራ እቅድ በማዘጋጀት ወደ ተግባር መግባቱንና የውሃ መሠረተ ልማት ዝርጋታ የመንገድ ሥራ መጠናቀቅን ተከትሎ የሚከናወን ተግባር መሆኑን አብራርተዋል።

የመንገድ መሠረተ ልማቱ እንደተጠናቀቀ የውሃ ዝርጋታና ስርጭት ፕሮጀክቱ የሚከናወን በመሆኑ የውሃ አቅርቦት ያላገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎች በዚህ ረገድ አገልግሎቱን ወዲያው እንደሚያገኙ ተናግረዋል።

በሌላ በኩል ለኮዬ ፈጬ ነባር ፕሮጀክቶች በቀን በአማካይ 25 ሺህ ሜትሪክ ኪዩብ ውሃ የሚቀርብ በመሆኑ በፈረቃ ለማዳረስ መገደዱን የገለጹት አቶ ፍቃዱ፤ ፍላጎትን የሚመጥን የውሃ አቅርቦት እስኪጀመር ነዋሪዎች በሳምንት ሁለትና ሶስት ቀን በፈረቃ የማቅረብ ሂደቱ እንደሚቀጥል አብራርተዋል።

የመብራት መቆራረጥ፣ የመስመር ብልሽት እንዲሁም በሌሎች የተለያዩ ምክንያቶች ውሃን ወደ ማኅበረሰቡ ለማድረስ የሚገድቡ በመሆኑ በፈረቃ የሚያገኙ አካባቢዎች ላይ በተቀመጠው ፈረቃ ላይ አንድ አንድ ጊዜ ተጨማሪ ተጽእኖ የሚፈጥሩ መሆናቸውን አቶ ፍቃዱ ተናግረዋል።



# መጤ አረሞች ሳይ ፈጣን እርምጃ ባለመወሰዱ ሥርዓተ ምህዳሩን እየጎዳ ነው

**ዳግማዊት ግርማ**

አዳማ፡- በተለያዩ መንገዶች ከውጭ ሃገራት የሚገቡ መጤ አረሞች ሳይስፋፉ እርምጃ ስለማይወሰድባቸው ሥርዓተ ምህዳሩን እየጎዱ እንደሚገኙ የኦሮሚያ ክልል ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ገለፀ።

በኢንስቲትዩቱ የግብርና ትራንስፎርሜሽን አስተባባሪ ዶክተር ሳሙኤል ቱፋ እንደተናገሩት፤ ከውጭ ሃገር የሚገቡ አረሞች ሳይስፋፉ እርምጃ ስለማይወሰድባቸው ሥርዓተ ምሕዳሩን እየጎዱ ነው።

እንደ ዶክተር ሳሙኤል ገለፃ፤ በተለያዩ መንገዶች ከውጪ ሃገራት የሚገቡት የአረም ዝርያዎችን ሳይስፋፉ እና አካባቢን ሳይጎዱ መቆጣጠር ቢቻልም እርምጃ ባለመወሰዱ ምክንያት በክልሉ አደገኛ መጤ አረሞች በሰብል እና በግጦሽ ቦታዎች ላይ ጉዳት እያስከተሉ ይገኛሉ።

የተከሰተውን መጤ አረም በፀረ-ተባይ ኬሚካሎች መከላከል እንደሚቻል የጠቆሙት ዶክተር ሳሙኤል፤ አደገኛ አረሞቹ ግን መሬት ውስጥ ለረጅም ጊዜያት ተደብቀው በመቆየት በድጋሚ የመራባት አቅማቸው ከፍተኛ መሆኑን ገልጸዋል።

አረሞቹ ብዛት ያለው ዘር የሚያፈሩና ባላቸው በአጭር ጊዜ አካባቢን የመውረር ባሕሪ ምክንያት እነሱ ባሉበት አካባቢዎች ሌሎች እፅዋት የማይበቅሉ በመሆናቸው በግብርናው ዘርፍ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደሩ እንደሆነም ዶክተር ሳሙኤል ገልጸዋል።

ከሌሎች እፅዋቶች ጋር አብሮ የመኖር ባህሪ የሌላቸው አረሞቹ የአካባቢውን የእፅዋት መብቀያ ስፍራዎችን በመውረር፣ የአፈሩንም ባሕሪያት በመቀየርና አካባቢውን ለተክሎች ምቹ እንዳይሆን በማድረግ የውኃ አካላትን እንደሚያደርቁም ዶክተር ሳሙኤል ተናግረዋል።

የአረም አይነቶቹ ከተለያዩ ሃገራት ከዕርዳታ እህል፣ ከውጭ በሚገቡ የማሽነሪ ዕቃዎች ጋር እና በሌሎች ምክንያቶች ወደ ኢትዮጵያ እንደሚገቡ የጠቆሙት ዶክተር ሳሙኤል፤ እነዚህ አረሞች በመንገድ ዳር፣ በማሳ ውስጥ እንደሚበቅሉም ተናግረዋል።

ቅድሚያ ተሰጥቶ አረሞቹ በትክክል እያደረሱ የሚገኙትን የጉዳት መጠን በተለይም በእፅዋት ላይ ምን ያህል ጉዳት እንደደረሰ፣ ምን ያህል ሄክታር መሬት በአረሞቹ እንደተወረረ እንዲሁም የአረሞቹን አይነት ብዛት ለማወቅ ደረጃውን የጠበቀ ጥናት መካሄድ እንደሚገባውም ዶክተር ሳሙኤል አሳስበዋል።

ዶክተር ሳሙኤል፤ በሕንድና አሜሪካ በመሳሰሉ የውጭ ሃገራት የትኛውም አይነት አስቸጋሪ አረም በተገኘበት ወቅት በፓርላማዎቻቸው ሁሉ ሳይቀር ምሕረት እንዳይደረግላቸው በማወጅ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የሚያስወግዱበት አግባብ እንዳለ ጠቁመው፤ በኢትዮጵያም መሰል አሠራሮች ተግባራዊ መደረግ እንዳለባቸው አመልክተዋል።



# የቅባት እህሉችን በስፋት በማምረት የዘይት ዋጋን ማረጋጋት እንደሚገባ ቋሚ ኮሚቴው አሳሰበ

አዲስ አበባ፡-የቅባት እህሎችን በአገር ውስጥ በስፋት በማምረት የዘይት ዋጋን ማረጋጋት እንደሚገባ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የኢንዱስትሪ እና ማዕድን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰበ።

ቋሚ ኮሚቴው ከሰሞኑ በኮከብ ቃና የዘይት ፋብሪካ የመስክ ምልከታ ባደረገበት ወቅት እንዳስታወቀው፤ የቅባት እህሎችን በሃገር ውስጥ በስፋት ማምረት ለዘይት ምርት የዋጋ መረጋጋት የተሻለ አስተዋፅዖ አለው።

ፋብሪካው የዘይት ምርት ለኅብረተሰቡ በስፋት የማቅረብ አቅም ያለው ቢሆንም፤ ባጋጠመው የግብዓት ዕጥረት ምክንያት በአቅሙ ልክ ማምረት እንዳልቻለ ቋሚ ኮሚቴው ከተደረገለት ገለጻ ተረድቷል።

ፋብሪካው የገበያውን ሁኔታ ለማረጋጋት እና የዘርፉን ምርታማነት ለማሳደግ፤ ከሌሎች ኢንዱስትሪዎች ጋር በቅንጅት መሥራቱን፣ ቋሚ ኮሚቴው በጥንካሬ ተመልክቷል።

ይሁን እንጂ የዘርፉን ምርታማነት አሁን ካለበት በተሻለ ለማሳደግ ግብዓት ሊያቀርቡ ከሚችሉ ድርጅቶች እና አርሶ አደሮች ጋር በበለጠ ቅንጅት መሥራት እንደሚያስፈልግ ጠቁሞ፤ ጥሬ ዕቃዎችን በሃገር ውስጥ ለማምረት በትኩረት ሊሠራ እንደሚገባ አሳስቧል።

ድርጅቱ በአጠቃላይ በግብይት ሥርዓቱም ሆነ በምርት ጥራት ደረጃው ላይ ቁጥጥር በማድረግ፤ የጀመረውን የገበያ ማረጋጋት ሥራ አጠናክሮ እንዲቀጥል ቋሚ ኮሚቴው በግብረ-መልሱ አሳስቧል።

የኮከብ ቃና የዘይት ፋብሪካ የአስተዳደር ዳይሬክተር አቶ ሚካኤል ካሳ እንዳስረዱት፤ በቀን 165 ቶን ዘይት የሚያጣራው ይህ ፋብሪካ፤ በዓመት አንዴ የሚያገኘው የቅባት እህል፣ ከሦስት ወር በላይ የሚያሠራው ባለመሆኑ፤ መሥራት ካለበት ከሃያ በመቶ በታች እየሠራ ይገኛል።

ድፍድፍ ዘይት ከውጭ በማስገባት እና በስፋት በማምረት፤ በተመጣጣኝ ዋጋ ለመንግሥት ሠራተኞች፣ ለሸማች ማኅበራት እንዲሁም ለተለያዩ የንግድ ተቋማት ምርቱን በማድረስ፤ የተከሰተውን የዘይት ዕጥረት ችግር ለመቅረፍ የተሻለ መሠራቱን ዳይሬክተሩ አያይዘው አብራርተዋል።

ዳይሬክተሩ አክለውም፤ የቅባት እህሎች በሚመረቱባቸው ቦታዎች ያለውን የጸጥታ ችግር በመፍታት፣ መንግሥት የበኩሉን ሚና እንዲወጣ እና የባንኮች ድጋፍም እንደሚያስፈልጋቸው ጠቁመዋል።

ዜና



ፎቶ ዳኜ አበራ

# ጽሕፈት ቤቱ የጓሮ አትክልቶችን በአነስተኛ ስፍራ ማልማት እንደሚቻል ለእናቶች ልምዱን አካፈለ

ጌትነት ምህረቴ

አዲስ አበባ፡- በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ለመመገብ የደረሱ ጎመን፣ ድንች፣ ሽንኩርት፣ ቆስጣ፣ካሮት ቀይስር፣ፎሶሊያና ሌሎች የጓሮ አትክልቶች በመስመር ተሰድረዋል።ቅጥር ግቢ ውስጥ በመስመር በመስመር ተተክለው የሚታዩት የጓሮ አትክልቶች አካባቢውን መናፈሻ አስመስለውታል። እነዚህ አትክልቶችና እንደ ቡና፣አቮካዶ፣ኮክ ያሉ ፍራፍሬዎች የግቢውን ውበት ማራኪና ሳቢ አድርገውታል ። በግቢው ውስጥ ትርፍ የሚባል ቦታ የለም።ግድግዳዎች እንኳ በሀይላንድ ዕቃ በተተከሉ የጓሮ አትክልቶች በመስመር ተሰድረውበታል።

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ አለምፀሐይ ጳውሎስ እንደገለጹት፤" ምግባችን በጓሯችን" በተሰኘው የጓሮ ግብርና እንቅስቃሴ በጠቅላይ ሚኒስትር ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚለሙ የጓሮ አትክልቶችን በማስጎብኘት እንዴት በአነስተኛ ቦታና ጠባብ ግቢ እንደ ቆስጣ፣ሰላጣና ጎመን ያሉ አትክልቶችን ማልማት እንደሚቻል ልምድ ማካፈል ተችሏል። በጉብኝቱና የልምድ ልውውጡ ላይ የተካፈሉ እናቶችም ይህን ልምድ ወስደው አትክልቶችን በትንሽ ቦታ ተክለውና ተንከባክበው በማሳደግ መጠቀም እንዲችሉ ያግዛል ።

ያለውን ትርፍ ቦታ ሁሉ ለከተማ ግብርና እናውል በሚል የተጀመረው ተግባር በአንድ ወር ከ15 ቀናት ውስጥ ፍሬ አፍርቶ አትክልቶቹ ለምግብ ደርሰዋል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤አትክልቶቹ ለዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ቢሰጡ በሚኖሩበት ስፍራ በትንሽ ቦታ ማልማት መጠቀም እንደሚቻል ተሞክሮ እንዲወስዱ ለማድረግ መሆኑን ገልጸዋል።

በጉብኝቱ ለተሳተፉ 55 እናቶችም በግቢው ውስጥ ለምተው የደረሱ አትክልቶችን እንዲጋሩ መደረጉንም ወይዘሮ አለምጸሐይ አስታውቀዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ያለንን ተካፍለን እርስ በእርስ ተሳስበን እንኑር ያሉትን ጥሪ ተከትሎ ጽሕፈት ቤቱ በግቢው ውስጥ ያለማቸውን የተለያዩ አትክልቶች ለእናቶች ማጋራቱንና ችግኞችን መስጠቱንም ሚኒስትር ዴኤታዋ ተናግረዋል።

ወይዘሮ መቅደስ በቀለ ከወረዳ 10 ጨርቆስ አካባቢ ነዋሪ ናቸው።በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ያዩት አትክልቶችና ፍራፍሬዎች በግቢው ውስጥ እንዲህ ማልማት ይቻላል እንዴ ያሚያስብሉ ናቸው ይላሉ።

ቅጥር ግቢው ውስጥ ትርፍ የሚባል ቦታ የለም።ግድግዳዎችና ግቢው ውስጥ የሚገኙ ባዶ ቦታዎች በአትክልቶችና በፍራፍሬዎች ለምተዋል የሚሉት ወይዘሮ መቅደስ፤ እኛም ከዚህ ትምህርት ወስደን በየግቢያችን እንተክላለን።እኔ የምኖርበት ብዙም ትርፍ ቦታ ስለሌለ በግድግዳዎች ላይ ሀይላንድ ዕቃ አትክልቶችን በመትከል ቢያንስ የአትክልት ፍጆታችንን ለመሸፈን እንሠራለን ብላለች።

የደረሱ አትክልቶችን ማካፈላችን ፍቅርን ማካፈል ነው ያሉት ወይዘሮ አለምጸሐይ፤ጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል በመኖሪያ አካባቢው አትክልቶችን እያለማ የምግብ ፍጆታውን መሸፈን እንዲችል ለማበረታታትና ልምድ ለማካፈል ያለመ መሆኑን አስታውቀዋል።



ፎቶ በጸሐይ ንጉሴ

# ‹‹ጽንፈኝነትን በየትኛውም መልክ፣ ቅርጽና መጠን ሁሉም እኩል ሊጠየፈው ይገባል››

-አቶ ክርስቲያን ታደለ

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- ጽንፈኝነትን በየትኛውም መልክ፣ ቅርጽና መጠን ሁሉም እኩል መጠየፍ ይገባዋል ሲሉ አቶ ክርስቲያን ታደለ ገለጹ።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የሆኑት አቶ ክርስቲያን ታደለ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ፤ ጽንፈኝነትን በየትኛውም መልክ፣ ቅርጽና መጠን ሁሉም እኩል መጠየፍ ይገባል።

‹‹በሃይማኖትም፣ በፖለቲካም፣ በየትኛውም ቁመና የጽንፈኝነት ቅዱስ የለውም፤ ይህንን በአጽንኦት ማመን መቻል አለብን። በኔ ስም እንዲህ እንድታደርግ አልፈቅድልህም ብሎ መጀመሪያ ማውገዝ ያለበት የሃይማኖት ተቋማት አባቶችና የእምነቱ ተከታዮች ናቸው›› ብለዋል።

የሃይማኖት ተቋማት የምርምር ተቋማት መሆን መቻል አለባቸው። የምንሰማው እንደምናስተውለውና እንደምንኖረው ሁሉም ሃይማኖቶች ሠላምን፣ በጎነትን፣ ቻይነትንና ትህትናን የሚያስተምሩ ናቸው። ሁከትና ብጥብጥን የሚያበረታታን ትውልድ የሃይማኖት አባቶች በስማችን አትነግዱ ብለው ማውገዝ አለባቸው። በሃይማኖት ተቋማት ስም የሚሠራ ወንጀል ካለ የእምነት አባቶች አልፈቅድልህም ማለት አለባቸው። ከሠላም እንጂ ከጠብ የሚያተርፍ ማንም የለም። ለመጾም፣ ለመስገድ፣ ለማምለክ ሠላም ያስፈልጋል። ኢትዮጵያ እንደ አገር በእስልምናም በክርስትና ሃይማኖትም በበጎ የምትነሳ አገር ናት። በጎ ታሪካችንን በጥላቻ እያጠፋነው ነው። ይሄ መቆም አለበት። ሲሉም መክረዋል።

የፖለቲካ ፓርቲ የተመሠረተው ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሻገር እንጂ ጥላቻ በመዝራት ግጭትን በመጥመቅ አሁን ካለንበት አስከፊ ሁኔታ ወደ ባሰ ሁኔታ ለማስገባት አይደለም ያሉት አቶ ክርስቲያን ግጭትን ለፖለቲካ ዓላማ ማስፈጸሚያ ማዋልን ሊያቆሙ ይገባል ብለዋል።

ዛሬ በግጭት ስልጣን ብንይዝ ነገ በግጭት እንወርዳለን ያሉት አቶ ክርስቲያን፤ ፖለቲካችን ሥር መሠረት እንዲይዝ፤ የሰለጠነ የፖለቲካ ባህልና ምህዳር እንዲሁም የዴሞክራሲ ተግባራት እንዲኖሩ ሠላም ያስፈልገናል ሲሉ ገልጸዋል። ለዚህም የሕግ የበላይነት እንደሚያስፈልግ ጠቅሰዋል። በተለይ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች የማይወዱትና እንዲቀየር የሚፈልጉት ሕግ እንኳን ቢሆን የማክበር ግዴታ አለባቸው ብለዋል። ነገ መንግሥት ሲሆኑ የሚያወጡት ሕግ ሊከበርላቸው በሚፈልጉት ልክ አሁን ላይ ያለውን ሕግ ጭምር የማክበር ግዴታ አለባቸው ሲሉም ገልጸዋል።

እንደ አቶ ክርስቲያን ገለጻ፤ ለዴሞክራሲ እታገላለሁ የሚሉ፤ የዴሞክራሲ ኃይል ነን ብለው ራሳቸውን የሰየሙ የፖለቲካ ፓርቲዎች ግጭትን ለፖለቲካ ዓላማ ማስፈጸሚያ ማዋልን ማቆም መቻል አለባቸው። ጨቋኝ ነው ብለው የፈረጁት አካል ሕግ እንዲያከብርም ምሳሌ መሆን መቻል አለባቸው። ሕግን እየጣሱ መንግሥት ሕግ እንዲያከብር መጠየቅ ግን ግብዝነት ይሆናል ሲሉም አመልክተዋል።

አቶ ክርስቲያን እንዳሉት፤ የጥላቻ አበጋዞች ፖለቲካን፣ ብሔርን፣ ሃይማኖትን እንደ ምሽግ እንዳይጠቀሙ መዝጋት ያስፈልጋል። እነዚህ ባዶ ሜዳ ላይ መጋለጥ መቻል አለባቸው። ይህ ሲሆን የጸጥታና የፍትሕ አካላትም ርምጃ ለመውሰድ ምቹ ሁኔታ ይፈጠርላቸዋል። ማኅበረሰቡ እነዚህን የጥላቻ አበጋዞችን ተው ብሎ መምከር፣ ለሕግና ለፍትሕ ማቅረብ መቻል አለበት።

አሁን ኢትዮጵያ ያለችበት ዐውድ ከበፊቱ የተለየ በመሆኑ፤ ሕዝቡም ሆነ የመንግሥትን ኃላፊነት የወሰዱ ሰዎች ይህንን ማወቅ እንዳለባቸው ጠቅሰዋል። ዛሬ ላይ "እስኪ እንየው" ተብለው የሚታለፉ ጉዳዮች የከፋ መከፋፈል እንዳያመጡ መጠንቀቅ እንደሚያፈልግም ጠቁመዋል። በዚህ ረገድ መንግሥት ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ መቻል እንዳለበትም ጠቅሰዋል።

በተለይ የጸጥታና ፍትሕ አካላትን የሚመሩ አካላት ቁርጥ ያለ ውሳኔ መወሰን መቻል እንዳለባቸውና የኢትዮጵያ አንድነትና የሕዝብ ደህንነት ቀይ መስመር መሆናቸውን በሚገባ ማመን እንደሚገባ አመላክተዋል። ሕጎች የሚወጡት ለመተግበር ስለሆነ የሕግ መተላለፍ ካለ መንግሥት የማስተግበር ግዴታ አለበት፤ ዜጎች ደግሞ በመንግሥት የሚወሰዱ ጸጥታን የማስከበርና ሠላምን የማስጠበቅ ርምጃዎች የማገዝ መብት እንዳላቸው ጠቁመዋል።



ፎቶ፡- ሐዲሽ አብርሃ

መሐመድ ፈረጂ



ሼህ መከተ ሙሄ



ኢብራሂም ከድር

# በረመዳን ወቅት የታዩ መልካም ተግባራትን ማስቀጠል እንደሚገባ ተገለፀ

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- በረመዳን ወቅት የታዩ የአንድነት፣ የመረዳዳት መልካም ተግባራትን እና ባህሎች በቀሪ ዕድሜ ሙሉ ሊቀጥሉ የሚገባቸው እንጂ የአንድ ቀን ተግባራት ሊሆኑ እንደማይገባ የእስልምና እምነት ተከታዮች ገለፁ።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያነጋገራቸው የእምነቱ ተከታዮች በረመዳን መልካም ነገሮችን የምንለማመድበት እና በሕይወታችን ቋሚ አድርገን የምንቀጥልበት ወር ነው ብለዋል።

ሼህ መከተ ሙሄ ያለፈውን የረመዳን ወር ሙስሊሙ ማኅበረሰብ በረመዳን ወር የመተባበር፤ የመተጋገዝ እና አብሮነትን ያሳየበት ወር እንደነበር አስታውሰዋል።

ሙስሊሙ ማኅበረሰብ ለድሆች፣ ለምስኪኖች እና አቅሞች ሲያጋራ ቆይቷል ያሉት ሼህ መከተ፤ መጋራትና መስጠት ዕውነተኛ ደስታ ስለሚሰጥ ሙስሊሙ ማኅበረሰብም ይህን ሲያደርግ በመቆየቱ ረመዳን ወር በዕውነተኛ ደስታ አልፏል ሲሉ ገልፀዋል።

ሆኖም በፆም ወቅት የታዩ የመረዳዳት፣ የመተጋገዝና የአንድነት መልካም ባሕርይዎች በቀሪ የሕይወት ዘመን ሁሉ ሊፈፀሙ የሚገባቸው እንጂ የአንድ ወር ብቻ አይደሉም ብለዋል።

አቶ ኢብራሂም ከድር በረመዳን ብዙ መልካምና በጎ ሥራዎች የሚከናወኑበት የፆም ወቅት መሆኑን አመልክተዋል ሙስሊም ማኅበረሰብ ከመጥፎ ተግባራት የሚጠበቅበትና መልካም ነገሮችን ያለምንም ግፊትና አነሳሽነት የሚሠራበት ወር ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ወሩ ሙስሊሙ ማኅበረሰብ አንድነቱን፣ መረዳዳቱንና መተሳሰብን ያሳየበት ወር ነበር፣ የረመዳን ወር ልክ እንደመለማመጃ ከፈጣሪ የተሰጠ ወር ነው። ስለዚህ መረዳዳቱ፣ መተጋገዙ፣ መተዛዘኑና በኅብረት መቆሙ ለአንድ ወር ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ጊዜያት መከወን ያለበት ነው ብለዋል።

ሕዝበ ሙስሊሙ በረመዳን ወቅት የተለማመደውንና ሲያደርግ የቆየውን አጠቃላይ ዕድሜውን በዚያ መልኩ እንዲያሳልፍ ይጠበቃል ሲሉም አሳስበዋል።

አቶ መሐመድ ፈረጂ በዘንድሮው ረመዳን ወር በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ዘንድ የነበረው የመደጋገፍና የመረዳዳት ስሜት የሚደነቅ ነበር ብለዋል።

በሰሜኑ ክፍል በነበረው ጦርነት ብዙዎች መጎዳታቸውና በተለያዩ አካባቢዎች ድርቅ መከሰቱ መረዳዳቱን እጅግ ወሳኝ ያደርገው ነበር ያሉት አቶ መሐመድ በረመዳን ወር ውስጥ የኢፍጣር ፕሮግራሞች የገጠር ከተሞችን ጨምሮ በብዙ ቦታዎች መካሄዳቸው ከፍተኛ የአብሮነት የመቀራረብ ስሜት እንደሚፈጥር ገልፀዋል።

አቶ መሐመድ፤ ያለፈው ረመዳን መረዳዳትና መደጋገፍ በአግባቡ የተተገበረበት ወር ነበር፤ በሃይማኖቱ አስተምህሮት መረዳዳትን፣ መደጋገፍና ይቅር መባባል በየትኛውም ጊዜ የሚደግፍና እንዲከናወን የሚፈለጉ ተግባራት መሆናቸውን አመልክተዋል።

በረመዳን የተሠሩ መልካም ነገሮች ሁሉ ቀጣይነት እንዲኖራቸው ይፈለጋል። ረመዳን በአንድ ወር ተከናውነው የሚያከትምላቸው መልካም ተግባራትን መተግበሪያ ወር ሳይሆን ከዚሁ ወር በልምምድ መልክ የወሰድናቸውን ሥልጠናዎች በዕድሜያችን ሙሉ የምናስቀጥልበት ብለዋል።




# የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አገልግሎት መሻሻል እንዳለበት ተጠቆመ

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አገልግሎት መሻሻል እንዳለበት ተጠቆመ፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ በጤና ሚኒስቴር እና በዓለም ጤና ድርጅት ትብብር የተሰራ ጥናት ይፋ በሆነበት ወቅት ነው ይሄ የተገለጸው፡፡

ጥናቱ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ ሥርዓት ላይ ያሉ ጠንካራ ጎኖችንና መሻሻል ያለባቸውን ነገሮች በመለየት እና በቀጣይ በትኩረት መሠራት ያለባቸውን ነገሮችን ለመጠቆም እንደሚረዳም ተገልጿል፡፡

የጥናቱ ዓላማ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት በጤና ጣቢያ ፣በጤና ኬላ፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ እና በከፊል በመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች የሚሰጡ ማኅበረሰብን ማዕከል ያደረጉ አገልግሎቶች በፋይናንስ በኩል ያላቸው ድጋፍ ምን እንደሚመስል ፣ በአመራሩ በኩል ያለው ትኩረት ምን ያህል እንደሆነ ፣አፈጻጸሙ ምን እንደሚመስል እንዲሁም የፍትሐዊነትን ጥያቄ በምን ያህል መልኩ እየተመለሰ ነው ለሚሉ ሀሳቦች ምላሽ ለመስጠት ነው፡፡

ጥናቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ኢትዮጵያ ያለችበትን ደረጃ እንዲሁም በአገር አቀፍ ደረጃ ክልሎች ያሉበትን ሁኔታ ለማየት እና በቀጣይ የሚሠሩ ሥራዎችን የጋራ የማድረግ ዓላማ እንዳለው ታውቋል፡፡

ጥናቱ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ ሥርዓት ላይ በፋይናንስ፣ በፍትሐዊነት እንዲሁም ከጥራት ጋር ተያይዞ ችግሮች መኖራቸውን አመላክቷል፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ ሥርዓት በፋይናንስ በኩል በሚፈለገው ደረጃ አጋሮች እገዛ እያደረጉ እንዳልሆነ፣ በፍትሐዊነት ረገድም አርብቶ አደር እና በመልክዓ ምድር ምቹ ያልሆኑ ቦታዎች ላይ ደከም ያለ መሆኑን ያሳየ ሲሆን በጥራት በኩል የዓለም የጤና ድርጅት ካስቀመጠው መስፈርት አንጻር የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ ከግማሽ ያልዘለለ እንደሆነ ጥናቱ አመላክቷል፡፡

በመድረኩ የተገኙት የጤና ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ደረጀ ድጉማ ጥናቱ ያመላከታቸውን ችግሮች ለመቅረፍ በቀጣይ የጤና ሚኒስቴር ከአጋር ድርጅቶች ፣ከክልሎች እና ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመወያየት የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ ሥርዓትን ለማሳደግ አቅዶ እንደሚሠራ ጠቁመዋል፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ ሥርዓትን ለማሻሻል የአስራ አምስት ዓመት ስትራቴጂ ማዘጋጀት አስፈላጊ እንደሆነ ጠቁመው፤ በየአምስት ዓመቱ ከጠቅላላ ዕቅድ እና ከመንግሥት ፖሊሲ ጋር በማዛመድ ማስቀጠል እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል፡፡

አመራሩ ትኩረቱን በሆስፒታሎች እና በከፍተኛ ደረጃ የሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ ብቻ ሳይሆን 80 በመቶ የሚሆኑ በሽታዎችን አስቀድሞ መከላከል ስለሚቻል የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ ስርዓትን ማሻሻል ላይም ትኩረት እንዲያደርግ እንዲሁም አጋር ድርጅቶች እገዛቸዉን ማሻሻል እንዳለባቸው ጠቁመዋል፡፡

# የኢትዮጵያ አንድነትና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ትውልድ ይፈጠራል፡፡

ባለፉት 30 ዓመታት እምነት አልባ እና አገር አልባ ትውልድ እንዲፈጠር መሠራቱን በማስታወስም፤ ትውልዱ አገሩን የሚወድ ፈጣሪውንም የሚፈራ አድርጎ የመቅረጽ የቤት ሥራ አለብን። ሥራ ፈጠራ ላይ ትኩረት ተደርጎ ካልተሰራ ኑሮ ውድነቱ ተባብሶ ይቀጥላል ሰላም፣ መረጋጋትና አንድነት ከተፈጠረ ኢትዮጵያን በፍጥነት ማሳደግ ይቻላል ብለዋል።

‹‹ሰላም ሚኒስቴር›› ስያሜው በጣም ቆንጆ ቢሆንም በተግባር ግን የሚጠበቅበትን ሚና ሊወጣ ይገባል።

በቅንነት ኢትዮጵያዊነት የሌለው ሰው በመንግሥት መዋቅርም ሆኖ ደባ ሊፈጽም ይችላል አሁን የሚታዩ አዝማሚያዎችን በጥንቃቄ መመልከት ያስፈልጋል። ሁሉም ለኢትዮጵያ በመታገል አብሮ ካልቆመ ሰላም ለማስፈን ያስቸግራል። በርካታ የቤት ሥራ ይቀረናል ሲሉም መክረዋል።

የዲፕሎማሲ ሥራ ላይ ለውጥ መምጣት አለበት። አረብኛ ቋንቋ የሚናገሩ አምባሳደሮች በመካከለኛው ምስራቅ ተመድበው ሁኔታውን መከታተል አለባቸው። የኢትዮጵያ እስልምና ጉባኤ በተጠናከረ መልኩ ተቋቁሞ ኢትዮጵያ በዓለም ሙስሊም ኅብረተሰብ ውስጥ ያላትን ከበሬታ ለመመለስ የሚያስችሉ ተግባራት ማከናወን ይጠበቅበታል።

ከሚታዩ ግጭቶች በስተጀርባ ማን ሊኖር ይችላል የሚለው ባግባቡ ሊጠና ይገባዋል። በዚህ ጉዳይ የታሪካዊ ጠላቶቻችን ሚና ምን እንደሆነ መታወቅ ይኖርበታል። ኢትዮጵያ የካርታ አቀማመጧን ብንመለከት ለመካከለኛው ምስራቅ ቅርበት ያላት ሆና እናገኛታለን ብለዋል።

ግብጾች ኢትዮጵያን ልክ እንደ ሶሪያና የመን ለማድረግ ቢሞክሩም ይከሽፍባቸዋል። አንድ ፋይል ሲዘጋባቸው ሌላ ፋይል ይከፍታሉ። ይህች አገር በሰላም እንድትኖር አይፈልጉም። በአገር መከላከያ ሠራዊት ሰሜን እዝ ላይ የተቃጣው ጥቃት ዝም ብሎ የተፈጠረ ሳይሆን የእነርሱ እጅ ነበረበት።

ግብጾች በዓረብኛ የሚተላለፉ አራት ሺህ ሚዲያ አላቸው። 80 ሺ ምሑራኖች በዓለም አቀፍ ተሰራጭተው ይገኛሉ። የዓባይ ጉዳይ ለእነርሱ ትልቅ ቦታ አለው፤ አንድ ግብጻዊ ከሕጻንነቱ ጀምሮ ያለዓባይ ሕይወት እንደሌለው፣ ከሰማይ የተሰጠ ትሩፋት እንደሆነ ያስተምሩታል በዓባይ የመጣ በሕይወታቸው እንደመጣም ይቆጥራሉ ነው ያሉት።

# ለዜጎች ስጋትን በሚፈጥሩ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ያለው መግለጫው፤ የስቅለት፤ የፋሲካ፤ የታላቁ የጎዳና ላይ ኢፍጣር፤ የኢድ አልፈጥርና የፍቼ ጫምባላላ በዓላት እንዲሁም ዓለም አቀፍ የሠራተኞች ቀንን ያስተናገድንበት ሳምንት እንደነበር አስታውሷል።

በዚሁ ወቅት በጎንደር ከተከሰተው አሳዛኝ ጥፋት እንዲሁም እሱን ተከትሎ በሌሎች አንዳንድ አካባቢዎች ላይ ከታየው ፍጹም ከኢትዮጵያዊነት ስነምግባር ያፈነገጠ ወንጀል ባሻገር በዓላቱ በመላ ሃገሪቱ በድምቀት ተከብረዋል። በዚህም በዓላቱ ኢትዮጵያውያን በፈተና ውስጥ ይበልጥ የሚጸና የአብሮነት እሴት እንዳላቸው ያሳዩበትና የሃገርንም ገጽታ ለመገንባት ያስቻሉ ናቸው ሲል መግለጫው አመልክቷል።

በሁሉም የሃገሪቱ ክፍል የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን ያሳተፉት እነዚህ በዓላት ከሃይማኖታዊ አስተምህሮታቸው ርቀው የጥፋት ማስተናገጃ እንዲሆኑ ለማድረግና በኢትዮጵያውያን መካከል የተዘረጋውን የአብሮነት ገመድ ለመበጠስ ያቀዱ ወንጀለኞች ብዙ ጥፋትን ለማድረስ በብርቱ የሞከሩበትም ወቅት መሆኑን መግለጫው አውስቶ፤ይህ ውጥናቸው ባሰቡት የጥፋት ልክና ባቀዱት የወንጀል ስፋት መጠን እንዳይሳካ ላደረጉት ኢትዮጵያውያን በሙሉ መንግሥት ከፍ ያለ ምስጋናውን ያቀርባል ብሏል።

ሕዝብ የሰጣቸውን ከፍተኛ ኃላፊነት በጠንካራ ቅንጅትና እስከ ሕይወት መስዋዕትነት ድረስ በመክፈል የተወጡ መላው የጸጥታ አካላትና ተባባሪ ተቋማትም ምስጋና ይገባቸዋል ያለው መግለጫው፤ለዜጎች በሰላም መኖር ስጋትን የሚፈጥሩ፤ በሃገር ሕልውና ላይም አደጋን የሚደቅኑ አካላት ላይ መንግሥት መውሰድ የጀመረውንም እርምጃ በተጠናከረ ሁኔታ እንደሚቀጥልም አስታውቋል።

በዚህ ሂደት ለጽንፈኝነትና አክራሪ አመለካከት ቦታ እንደሌለው በተግባር ያረጋገጠው መላው ሕዝብ ከሰሞኑ እንደታየው ወንጀለኞችን አጋልጦ በመስጠትና ከጸጥታ አካላት ጋር በመተባበር ያሳየውን ተሳትፎ አጠናክሮ እንዲቀጥል መንግሥት ጥሪውን ያቀርባል ሲል የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት በመግለጫው አስታውቋል።

## ሕወሓት እያደረሰ ያለው መከራ እንዲያበቃ የትግራይ ልሂቃን ድምጻቸውን እንዲያሰሙ ትዴፓ ጠየቀ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- ሕወሓት በትግራይ ሕዝብ ላይ እያደረሰ ያለው መከራ እንዲያበቃ የትግራይ ልሂቃን ድምጻቸውን እንዲያሰሙ የትግራይ ዴሞክራሲዊ ፓርቲ (ትዴፓ) ጠየቀ።

የትግራይ ዴሞክራሲዊ ፓርቲ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ሙሉብርሃን ኃይሌ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሕወሓት በ1977 ዓ.ም በተከሰተው ድርቅ ምክንያት ለትግራይ ሕዝብ የተላከን እርዳታ ለመሳሪያ መግዢያ ሲያደርግ የነበረ የትግራይ ሕዝብ ቀንደኛ ጠላት ነው።

አሁንም ከስልጣን ተገፍቶ በመሄድ የትግራይን ሕዝብ እንደምሽግ በመጠቀም በሕዝቡ ላይ ከፍተኛ የሆነ ግፍ እየፈጸመ ነው ያሉት ኃላፊው፤ ከመንግሥትና ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት የሚላከውን የሰብዓዊ እርዳታ የሽብር ቡድኑ ለራሱ ጥቅም እያዋለው ነው።

እንደ አቶ ሙሉብርሃን ገለጻ፤ በትግራይ ሕዝብ ስም የሚነግደውንና በሕዝቡ ላይ እየፈጸመ ያለውን ሁለንተናዊ ግፍ ለትግራይ ህዝብ ተቆርቋሪ ነን የሚሉ ልሂቃንና ዲያስፖራዎች እውነቱን በመረዳት ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ሊያስረዱ ይገባል። አሸባሪ ቡድኑ የሚላከውን የሰብዓዊ እርዳታ ለሕዝቡ መስጠቱ ቀርቶ ሕዝቡ ካለው እንዲያወጣ እያስገደደ ነው። የምናዋጣው የለንም የሚሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች ለእስራት፣ ለድብደባና እንግልት እየተዳረጉ መሆኑን አንስተዋል።

ሕወሓት እየተከተለው ያለው አካሄድ የትግራይ ሕዝብ እንደ ሕዝብ እንዳይኖርና እንዲጠፋ ነው ያሉት የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው፤ ልሂቃኑና ዲያስፖራው ሕወሓት እየተከተለ ያለውን አደገኛ አካሄድ በመገንዘብ ድምጽ ለተነፈገው ሕዝብ ድምጽ ሊሆኑ ይገባል ብለዋል።

የትግራይ ልሂቃንና የትግራይ ተወላጅ የዲያስፖራ አባላት አሸባሪ ቡድኑ በሕዝቡ ላይ እያስከተለ ያለው ሁለንተናዊ ግፍ ገብቷቸው ሕዝቡን ለማዳን ድምጻቸውን ሊያሰሙ እንደሚገባም ጠቁመዋል።

በመንግሥትም ሆነ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ረጂ ድርጅቶች አማካኝነት ወደ ትግራይ የሚላከው የሰብዓዊ እርዳታ ለትግራይ ሕዝብ እየደረሰ እንዳልሆነ ትዴፓ እንዳረጋገጠ የገለጹት የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው፤ ለትግራይ ሕዝብ እናስባለን የሚሉ የትግራይ ልሂቃንና ዲያስፖራዎች ድምጻቸውን እያሰሙ አይደለም። የትግራይ ሕዝብ እየጠፋ በዝምታ መመልከታቸው ታሪካዊ ስህተት እየፈጸሙ መሆኑን ሊያውቁ ይገባል። ሕወሓትን ለማዳን ሲባል የትግራይ ሕዝብ መጥፋት እንደሌለበትም ገልጸዋል።

የትግራይን ሕዝብ ራሳቸው እየሙቱ መቺ እየፈጠሩ በተዛባ መረጃ እንዲደናገር በማድረግ ወደ ጦርነት እያሰለፉት ነው። የትግራይ ሕዝብም እንደ ሕዝብ ከዚህ በላይ ሊሸከማቸው አይገባውም፣ በቃህ ሊላቸው እንደሚገባ አቶ ሙሉብርሃን አሳስበዋል።

አንድ አሸባሪ ሽፍታ ቡድንን ለማዳን ሲባል የትግራይ ሕዝብ መጥፋት የለበትም ያሉት አቶ ሙሉብርሃን፤ በተለያዩ መስኮች የተሠማሩ የትግራይ ተወላጆች እየሆነ ያለውን በመገንዘብ ድምጻቸውን ማሰማት አለባቸው ብለዋል።

ለትግራይ ሕዝብ እናስባለን የሚሉ ልሂቃን ድምጻቸውን ለሕዝቡ እያሰሙ አለመሆኑን የጠቆሙት አቶ ሙሉብርሃን፤ በትግራይ ሕዝብ መድኃኒትና የተለያዩ የምግብ እርዳታ እየገባ ቢሆንም በትክክል ለሕዝቡ ባለመድረሱ በተለያዩ በሽታዎችና ረሃብ እንዲጋለጥ ሆኗል ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሰላምና ደህንነትን የማረጋገጥ ሥራው ጊዜ ሊሰጠው አይገባም!

ሰላም መቼም ቢሆን ከምንም በላይ አስፈላጊና ወሳኝ ጉዳይ ነው። ያለ ሰላም ምንም መሆን አይቻልም። ዕቅድ የሚታቀደው ፣ ምኞትና ተስፋ ማለም የሚቻለው ሰላም ሲኖር ብቻ ነው ። በጥቅሉ ሁሉንም ነገር ማድረግ የሚቻለው ሀገር ሰላም ሲሆን ነው። ስለዚህ የሰላም ጉዳይ ጊዜ የሚሰጠው ሳይሆን፣ ከምንም ነገር በላይ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ መሆን አለበት።

መንግሥት በሀገር ላይ ሰላምን የማስከበር ፣የዜጎችን ደህንነት የመጠበቅና የማስጠበቅ ኃላፊነትም ግዴታም አለበት። ይሄንን ኃላፊነቱን በሚገባ ሊወጣ ይገባል። እስካሁን ባለው ሁኔታ በሀገራችን በተለያዩ ምክንያቶች የሰላም መደፍረስ ታይቷል። ብዙዎች ከውስጥም ከውጭም ተቀናጅተው የሀገርን ሰላም ለማናጋት ተንቀሳቅሰዋል። አንዴ በብሄር ፣ሌላ ጊዜ በሃይማኖት ለእያንዳንዱ ግጭት ስም በመስጠት የህዝብን ሰላም የሚያደፈርሱ ችግሮችን አስተናግደናል። ሀገር ተረጋግቶ፣ ዜጎች በሰላም ወጥተው እንዳይገቡ ብዙ መሰናክሎች ተደቅነው አልፈዋል። በሂደቱም የዜጎች ህይወት ጠፍቷል፣ ንብረት ወድሟል፤ በርካቶች ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል። ይሄ አሳዛኝ ክስተት አሁንም ቀጥሏል። መንግሥትም አንዴ ጠንከር ሌላ ጊዜ ለስለስ በማለት ችግሮችን በሰከነና በሰለጠነ መንገድ ለመፍታት ሞክሯል። መሰናክሎችን በትዕግስት በማለፍ ዛሬ የደረስንበት ደረጃ ደርሷል።

ይሁን እንጂ የጸብ ደጋሾች ድግስ አሁንም አልተገታም። በጠላቶች ሴራና በውስጥ ባንዳዎች ተባባሪነት ኢትዮጵያን የማተራመስ እንቅስቃሴው ቀጥሏል። ሰሞኑንም አንዱን ሃይማኖት በሌላው ላይ ለማነሳሳት የሚደረገውን ሴራ ህዝብ በሚገባ ሊያውቀው ይገባል። ሃይማኖቴ ተነካ ፣ መስጊድ ወይም ቤተክርስቲያናት ሊያፈርሱ ነው ከሚለው የቅድመ ቃላት ዘመቻ ጀርባ ማን ምን እያደረገ ነው የሚለውንም ጠንቅቆ መረዳት ይገባል። ህዝብን ለእልቂት የሚዳርግ የሴራ ጥንስስ ነው ብሎ ቆም ብሎ ማሰብ ይገባል። እያንዳንዱ ድምጽ ባሰማ ቁጥር አብሮ «ሆ» ብሎ የሆያሆዬው አካል ከመሆን ይልቅ ረጋ ብሎ ማሰብ ይገባል። ሰላም የሚገኘው በሆታ ሳይሆን ከመንግሥትና ከህዝብ ጋር በመነጋገርና በመወያየት የሆያሆዬውን ምንነት ለመረዳት በመሞከርና ለሆታው ተገዢ ባለመሆን ብቻ ነው።

ዛሬ የኢትዮጵያ ጠላቶች ሀገር ለማፍረስ የማይፈነቅሉት ድንጋይ አይኖርም። በተለያዩ ማህበራዊ ድረገጾች እየፎከሩና አንድነታችንን በመሸርሸር ሀገርን ለማተራመስ እንደሚሰሩ ሲገልጹም ተደምጠዋል። ታሪካዊ ጠላቶቻችን እርስ በእርስ ስንታመስ መግቢያ በር እንደሚያገኙ ያስባሉ። የታሰበው ልማት ሁሉ አፈር ከድሜ እንደሚገባ ያውቃሉ። ከፍተኛ ወጪ ወጥቶባቸው ጉልበትና ጊዜ ፈሶባቸው የተሰሩት ልማቶች ሁሉ እንደሚፈርሱ ያውቃሉ። በዚህ መካከል ተጠቃሚ እንደሚሆኑ በማሰብ በሁሉም የእምነት ተቋማት መካከል ቅጥረኞችን በማደራጀት፣ ህዝብ ከህዝብ ፣ ህዝብን ከመንግሥት ጋር ለማጋጨት አበክረው ይሰራሉ።

አሁን እያየን ያለው የሃይማኖት ግጭት የሚመስል የሰላም መደፍረስ የዚሁ ዕቅድ አንዱ አካል ስለመሆኑ እማኝ ማቅረብ አይጠይቅም። በእስካሁኑ ሂደቶች የተረጋገጡት እውነታዎች ለዚህ እማኝ ናቸው። ህዝቡም ይሄንን በሚገባ ማወቅ አለበት። የዚህ ሴራ ሰለባ ላለመሆን ደግሞ ከሆታ ይልቅ በሰከነ መንፈስና በእርጋታ ነገሮችን አጢኖ ራሱን ከችግር ተባባሪነት ማውጣት አለበት። ለጥፋት ሳይሆን ለሰላም መሰለፍ ይገባል።

ሕዝብ ይሄን ከተወጣ፣ መንግሥትም ሀገርን እና ህዝብን በሚያተራምሱና ሰላም በሚነሱ አካላትና ተላላኪዎች ላይ ጠንከር ያለና የማያዳግም እርምጃ ሊወስድ ይገባል። እስካሁን ብዙ ነገሮች በሆደ ሰፊነትና በትዕግስት ታልፏል። ሆኖም ትዕግስቱን በልኩ የሚገነዘብ ባለመኖሩ ችግሩ ሲብስ እንጂ ሲሻሻል አልታየም። በመሆኑም ትዕግስት ፍራቻ መስሎ ለሚሰማቸው አካላት ትዕግስትም ልክአለው መባል አለባቸው። መላው ህዝብም አሁን በሀገራችን እያየንና እየሰማናቸውና እያየናቸው ያሉትን የሰላም መደፍረሶች የታሪካዊ ጠላቶቻችን እቅድ መሆናቸውን በሚገባ በመገንዘብ ወደግባቸው ለመሄድ የሚያደርጉትን ጉዞ ከወዲሁ መግታት ይገባል።

ኢትዮጵያ የአንድ ብሄር ወይም የአንድ ሃይማኖት ሀገር አይደለችም። የሃይማኖትና የብሄር ብዝሀነት የምታስተናግድ አንዱ ከሌላው ወገኑ ጋር ልዩነቱን አምኖ፣ ተከባብሮና ተፋቅሮ የሚኖርባት ሀገር ናት። አንዱ ላንዱ ስጋት ሳይሆን ስጋው ሆኖ የኖረበትና አሁንም የሚኖርበት ሀገር ናት። አሁንም ማስቀጠል ያለብን ይሄንኑ አንድነታችንን ነው። ወደፊትም ማስቀጠል ያለብን በብዝሀነትና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ወንድማማችነትን ነው። ሀገር እንደሀገር እንድትቀጥል በቅድሚያ ከጠላቶቻችን ወጥመድ መውጣት መቻል አለብን። ከዚህ ወጥመድ መውጣት የምንችለው ደግሞ የሀገራችንን ሰላም ማክበርና ማስከበር ስንችል ነው ። መንግሥትም ትዕግስትም ልክ አለው ብሎ ሰላምን ለማስከበር በአጥፊዎቹ ላይ ያልተቆጠበ ቆራጥ እርምጃ መውሰድ ሲችል ነው። የሚፈለገው ሁሉን አቀፍ ብልጽግናን ለማረጋገጥም ቢሆን ሰላምን ማስከበር የግድነውና ሰላምና ደህንነትን የማረጋገጥ ሥራው ጊዜ ሊሰጠው አይገባም!


አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## በተግባር የተደገፈ እቅድ የሚፈልገው የህዝብ ጥያቄ

**አምኃየስ መርዕድ**

ሀገር በህዝቦች አንድነትና ስምምነት የሚመሰረት እንደመሆኑ ህዝቦችን የሚያስተዳድር መንግሥትም ከህዝብ የሚወጣና በህዝብ የሚመረጥ ነው። መንግሥት ደግሞ ህዝቡን የሚያስተዳድርበት ህገ መንግሥት አውጥቶ ወደ ሥራ ይገባል። ይሄ በሁሉም የዓለም ሀገራት ተግባር ላይ የዋለ ነው። በኢትዮጵያም በአፄ ኃይለስላሴ ስርዓተ መንግሥት የመጀመሪያው ህገ መንግሥት መዘጋጀቱ ይነገራል። ከዛም በኋላ ሀገሪቱን ያስተዳደሩት መንግሥታት የራሳቸውን የአስተዳደር እሳቤ የሚያንፀባርቅ ህገ መንግሥት አዘጋጅተዋል። በአሁኑ ወቅት ሥራ ላይ የዋለው ህገ መንግሥት በ1987 ዓ.ም የተዘጋጀው ነው።

በኢፌዴሪ ህገመንግሥቱ አንቀፅ 32 (1) "ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሀገሪቱ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የመመስረት እንዲሁም በፈለገው ጊዜ ከሀገር የመውጣት ነፃነት አለው" ይላል:: አንቀፅ 40 (1) ደግሞ "ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሀገሪቱ ውስጥ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራት፤ ለመተዳደሪያው የመረጠውን ሥራ የመስራት መብት አለው" ይላል። በተጨማሪም በህገ መንግሥቱ አንቀፅ 30 ላይ ዜጎች ከሀገሪቱ የመንግሥት አካላት ማግኘት ስላለባቸው መሰረታዊ መብቶች ይዘረዝራል። የመኖር መብት፣ የአካል ደህንነት መብቶች፣ የመሰብሰብና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብቶች እንዲሁም ንብረት የማፍራትና ኢኮኖሚያዊ መብቶች ይጠቀሳሉ።

በአንቀፅ 13 ንኡስ አንቀፅ አንድ ላይም በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የፌዴራል መንግሥትና የክልል ህግ አውጪ፣ ህግ አስፈፃሚና የህግ ተርጓሚ አካላት እነዚህን መብቶች እንዲያከብሩና እንዲያስከብሩ ኃላፊነትና ግዴታ ተጥሎባቸዋል። እነዚህ ጉዳዮች በህገ መንግሥቱ ይቀመጡ እንጂ በተግባር ግን በአስፈፃሚ አካላት ትኩረት ተሰጥቷቸው እየተሰሩ አይደለም።

በሀገሪቱ የለውጥ አራማጅ መንግሥት ከመምጣቱ ሁለትና ሶስት ዓመታት በፊት ህብረተሰቡ በመልካም አስተዳደር እጦት ተማሮ እንደነበር አይዘነጋም። በወቅቱም መንግሥት ሰፊ ህዝባዊ ውይይቶች አድርጎ ሙስና፣ የኑሮ ውድነት እንዲሁም የሰላም እጦት መንሰራፋቱና መፍትሄ እንዲሰጣቸው በህብረተሰቡ በኩል በጥያቄነት ቀርቦ ነበር። መንግሥትም አፋጣኝ ርምጃ እንደሚወስድ ቃል ገብቶ፤ እቅድ አውጥቶ ወደ ተግባር ገብቻለው አለ። ነገር ግን መፍትሄ ከመስጠት ይልቅ ችግሩ በመባባሱ በለውጥ መንግሥት እንዲተካ ሆኗል።

የለውጥ መንግሥቱም የነበረውን ችግር በሂደት ፈትቶ መልካም አስተዳደር እንደሚያሰፍን ቃል በመግባትና ይቅርታ በመጠየቅ ወደ ማስተዳደሩ ገባ።

ከለውጡ ማግስት በሀገሪቱ በተካሄደው ስድስተኛው ሀገራዊ ምርጫም የብልፅግና ፓርቲ መንግሥት መመስረቻ ድምፅ አግኝቶ በህጋዊ መንገድ ህዝብ በማስተዳደር ላይ ይገኛል። ፓርቲው የመጀመሪያውን ጉባኤ ባካሄደበት ወቅት ከህዝብ የሚነሱ ጥያቄዎችን ለመመለስ ቅድሚያ ሰጥቶ መስራት እንዳለበት በመወሰኑ ከጉባኤው ማግስት ጀምሮ ህዝባዊ ውይይቶች ተደርገዋል።

በውይይቶቹም የመንግሥት አካላት ህዝቡ በውይይቶቹ ያነሷቸውን የመሰረተ ልማት፣ የመልካም አስተዳደር፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ፣ የሰላምና ፀጥታ፣ የህግ የበላይነት እና የሥራ እድል ፈጠራ በቀዳሚነት ለመመለስ ጥረት እንደሚያደርጉ ጠቅሰዋል። በተጨማሪም የኑሮ ውድነትና የመልካም አስተዳደር እንዲሁም ሰላምና ፀጥታ ጉዳይ አስቸኳይ እልባት ለመስጠት እቅድ ማቀዳቸውን በሚሰጡት መግለጫዎች ማየት ይቻላል። ህዝቡ ያነሳቸው ጥያቄዎች እቅድን ሳይሆን ትግበራን የሚፈልጉ ስለመሆናቸው ነጋሪ አያሻም። ህብረተሰቡ ሰላምና መረጋጋትን አጥብቆ እንደሚፈልግ በየመድረኩ ሀሳቡን ገልጿል። በየጊዜው እየጨመረ የመጣው የኑሮ ውድነትም እንዲሁም በተለያዩ መንገዶች እንዲፈቱለትም ጠበቅ ያለ ጥቄውን አቅርቧል።

ህዝብ ያስተዳድረኛል የሚለውን ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ሲመርጥ ያለበትን ችግሮች እንዲፈታለት እንጂ ተመራጮቹ ሲሽሞኖሞኑ ለማየት አይደለም። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በተለያዩ አካባቢዎች የፀጥታ ችግር እየተስፋፋ ነው። አንዳንዶቹ የህዝብ ተሿሚዎች በማህበራዊ ትስስር ገፃቸው ፅንፈኝነትን ሲያራግቡና ግጭት የሚፈጥሩ እንደሚውሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ስልጠና በሰጡበት ወቅት በግልፅ ተናግረዋል። ታድያ እነዚህን አይነት የተመራጭ ቀላጆች ባሉበት የህዝብ ጥያቄ ለመመለስ እቅድ ቢቀመጥ ችግር ይፈታል ማለት ዘበት ነው። ምክንያቱም ችግር አምጪ አመራር ችግር ፈቺ መሆን ስለማይችል ነው።

ሌላው በየመድረኩ የህዝብ ጥያቄ የነበረው የኑሮ ውድነት ነው። በሀገሪቱ ኑሮ በየጊዜው እየጨመረ ነው። ለዚህ ደግሞ ከስግብግብ ነጋዴው እኩል የሰላም እጦት በምክንያትነት ይጠቀሳል። በዚህም መሰረታዊ የሚባሉ ሸቀጦች ዋጋቸው እየናረ ነው። አርሷአደሩ ከማሳው ጀምሮ በደላላዎች ዋጋ እየተተመነ ወደ ገበያ የሚቀርብበት አሰራር መንግሥት ካላቆመ ኑሮው ይበልጥ እንደሚወደድ ህዝብ ለመንግሥት በየመድረኩ ተናግሯል። መንግሥትም ችግሩን በግልፅ ያውቀዋል። ነገር ግን በእቅድ እፈታዋለው ብሎ ከማሰብ እቅዱን በተግባር ቢደግፈው ለውጥ ማምጣት ይችላል።

በሀገሪቱ ሰላም ለማምጣት ከመንግሥት እኩል የህብረተሰቡ ትብብር ይፈልጋል። ህብረተሰቡ እርስበርስ በመተባበር የጥፋት አላማ ያላቸውን ሰዎች መታገል ካልቻለ መረጋጋት ሊመጣ አይችልም። በሌላ በኩልም አንድነትን የሚሸረሽሩ ጉዳዮች ሲገጥሙት የመነጋገር ባህል ማዳበር ካልቻለ የሰላም እጦት ይፈጠራል። በዚህ ደግሞ ከኑሮ መወደድ ባሻገር የመኖሪያ ስፍራም የሚታጣበት ሁኔታም እንደሚኖር ግምት ውስጥ መግባት አለበት።

ባለፈው አንድ ዓመት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተቀሰቀሰው ጦርነት ምክንያት ብዙ ሰው ተፈናቅሏል። ለአካል ጉዳትም ተዳርጓል። ይህ ሁኔታ ቀድሞ የነበረውን የሀገሪቱ የድህነት ሁኔታን አባብሶታል። በተለይ የሥራ አጥ ወጣቶች ቁጥር እየበዛ መምጣት በየጊዜው ለሚፈጠሩት የሰላም መደፍረሶች አንድ ምክንያት ይሆናል። ሀገር የመበጥበጥ ተግባር ውስጥ የተሰማሩ ሰዎች ወጣቶቹን መጠቀሚያ እያደረጉ ናቸው። በሌላ በኩልም የመልካም አስተዳደር እጦትና የህግ የበላይነት አለመኖር ወጣቱ ወደ ጥፋት እንዲገባ እየገፋው ይገኛል። የመልካም አስተዳደር ችግር መስፋፋቱ በማሳያነት የሚቀመጠው ሙስና ነው። በአሁኑ ወቅት ጉቦ ሰጥቶ ጉዳዮችን ማስፈፀም እንደ ግዴታ ተቆጥሯል። ይህ ሁኔታ ደግሞ በተደጋጋሚ በመገናኛ ብዙኃን በኩል የቅሬታ ዜና ቢሰራበትም መሰረታዊ የሆነ ለውጥ ግን አልታየም። በመንግሥት አገልግሎት መስጫ ተቋማት ውስጥ እንደ ባህል እየተስፋፋ የሚገኘውን ‹‹እጅ መንሻ›› ገንዘብ መንግሥት አፋጣኝ የተግባር መፍትሄ ካልሰጠበት የሚያመጣው ጉዳት ከፍተኛ ነው።

እንደ አጠቃላይ በሀገሪቱ በሁሉም ቦታዎች የሚገኘው ህዝብ በአንድ ቃል ሰላም እንዲሰፍንለት ጥያቄውን አቅርቧል። በተጨማሪም የመልካም አስተዳደር ችግር፣ የኑሮ ውድነት እንዲሁም ሙስና በአፋጣኝ መፍትሄ እንዲሰጣቸው አሳስቧል። ዝም ያለ ህዝብ ደግሞ ሲነሳ ምን ሊመጣ እንደሚችል መገመት ከባድ ስለማይሆን ተመራጩ መንግሥትም የህዝቡን ጥያቄ ተቀብሎ ወደ ተግባር መግባት አለበት።

# ተጠየቅ

# “የሀገራችን ኢኮኖሚ ያለበት ሁኔታ ጤናው የተጓደለ ነው፤ ነገር ግን መታከም ይችላል”

*-ፕሮፌሰር መንግስቱ ከተማ*
*የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ አሶሴሽን ዋና ሥራ አስፈፃሚ*

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ አሶሴሽን ለትርፍ ያልተቋቋመ፤ ከፖለቲካ እና ሃይማኖት ገለልተኛ የሆነና 5ሺ400 አባላትን ያቀፈ የሙያ ማህበር ነው። ዓላማዎቹም በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ፖሊሲ አማራጮች ላይ ጥናትና ምርምሮችን በማካሄድ ለፖሊሲ እና ኢንቨስትመንት ውሳኔ የሚረዱ የመረጃ ግብዓት መስጠት፤ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎችን የሙያ ፍላጎቶችና ጥቅሞች እንዲጎለብቱ ማገዝ፤ የምርምር ውጤቶች በኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲሰራጩ ማድረግ፣ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ዝግጅትና ትግበራን የሚያግዙ ስልጠናዎችን መስጠት፤ ሀገራዊና ኢኮኖሚ ጉዳዮች ላይ የውይይት መድረኮችን መፍጠር እና በኢትዮጵያ ውስጥ እና በውጭ ሀገር ባሉ የምጣኔ ሃብት ባለሙያዎች መካከል ሙያዊ ግንኙነት እንዲዳብር ማበረታታት ናቸው።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ አሶሼሽን ለሚያቀርባቸው ትንታኔዎችና ጥናቶችም በዋናነት የማዕከላዊ ስታትስቲክስ፣ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ፣ ዓለም ባንክ፣ የተባበሩት መንግሥታት የምግብና የእርሻ ድርጅት፣ ኢንዱስትሪ ልማት ድርጅት እና ሌሎችን የመረጃ ምንጮች በዋናነት ዋቢ አድርጎ ይጠቀማል። የዝግጅት ክፍላችንም ከአሶሴሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ፕሮፌሰር መንግስቱ ከተማ ጋር የሀገሪቱን ወቅታዊ የኢኮኖሚ ጉዳዮችን አስመልክቶ ቆይታ አድርጓል። መልካም ንባብ።



**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ አሶሼሽን የሚያካሂዳቸው ጥናቶች ምን ላይ ያተኩራሉ?**

**ፕሮፌሰር መንግስቱ፡-** የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊ መዋቅር የሚዳስስ በተለይም ደግሞ ከዋጋ ግሽበት ጋር በተያያዘ ምን ላይ ማተኮር ይገባል የሚለው ጉዳይ ላይ ጥናት ተካሂዷል። ከዚህም በተጨማሪ በኢኮኖሚ ጋር ዝምድና ያላቸው በርካታ ጉዳዮችን ይዳስሳል። በዚህ ውስጥ የሀገሪቱ ምጣኔ /ሃብት ጤናማ ሆኖ እንዲቀጥል የራሱን ድርሻ የሚወጣ ይሆናል። ጥናቶቹ የሚለኩት ባላቸው ሀገራዊ ፋይዳ እና ዜጎች ተጠቃሚ መሆን በሚገባቸው አንኳር ጉዳዮች ላይ ነው። ለፖሊሲ አውጪዎችም እንደ ግብዓት ሆኖ የሚያገለግል ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት የሚስተዋለው የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ጤናማ ነው?**

**ፕሮፌሰር መንግስቱ፡-** አሁን አገሪቱ ያለችበትን ሁኔታ ስንገነዘብ ኢኮኖሚው ያለበት ሁኔታ ጤናው የተጓደለ ነው፤ ነገር ግን መታከም ይችላል። ጤናው የተስተጓደለ ነው የምንለው በርካታ ችግሮችን እያለፈ በመሆኑ ነው። በመጀመሪያ ኮረና ቫይረስ ወረርሽኝ ነበር። በሁለተኛ ደረጃ በሀገሪቱ ውስጥ የነበረው ግጭት አደገኛና በኢኮኖሚው ላይ ትልቅ ጫና የፈጠረ ነው። በሦስተኛ ደረጃ በሀገሪቱ ቆላማ አካባቢዎች የተከሰተውን ድርቅ ነው።

በአሁኑ ወቅት ደግሞ የራሺያ እና ዩክሬን ጦርነት በሀገራችን ምርቶች ላይ ያስከተለው የዋጋ ጫናም ከፍተኛ ነው። ሀገሪቱም ከፍተኛ የዕዳ ጫና አለባት። የገቢ እና ወጪ ንግድ ሚዛንም የተጣጣመ አይደለም። የመንግሥት በጀት፣ የመንግሥት ወጪ እና ገቢው ሲታይም ያልተጣጣመ ነው። ሙስናም የተንሰራፋበት ሁኔታ ይታያል። እነዚህ ሁኔታዎችን ደምረን ስናይ ጤናማ ነው ማለት ይከብዳል።

**አዲስ ዘመን፡- ኢኮኖሚው መታከም የሚችል ነው ብለዋል። ችግሩ በምን ደረጃ ይገለፃል?**

**ፕሮፌሰር መንግስቱ፡-** የዋጋ ግሽበቱ ቢታይ በጣም ከፍ ያለ ነው። ጥቅል የዋጋ ግሽበቱ 33 ከመቶ ነው። የምግብ 43 ከመቶ ደርሷል። ይህ ትልቅ ተፅዕኖ ፈጥሯል። በተለይ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው፣ ምንም ገቢ የሌላቸው እና በጡረታ በሚተዳደሩት ላይ በጣም ጫና ይፈጠርባቸዋል። ይህ ሁኔታ ሄዶ ሄዶ ወደ ንጥቂያ ሊያመራ እና ዘረፋ ሊስፋፋ ይችላል። ወንጀሎችም ሊበራከቱ ይችላሉ። ህዝብ ውስጥ ከፍተኛ ብሶት አለ። ነገር ግን በሌላ ሀገር የሚታየው ህገ ወጥነት አይታይም። የኢትዮጵያ ህዝብ ታጋሽ ነው። ህዝብ መንግሥት ያለፈበትን የጦርነት ሁኔታ፣ የኮረና ቫይረስ ስርጭት የፈጠረውን ጫና በመገንዘብ መንግሥትን መፍትሄ ያመጣል በማለት በመጠበቅ ላይ ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- በፆታ ረገድስ የኑሮ ውድነቱ ሴቶች ላይ የሚፈጥረው ተጽዕኖ በጥናት ለማካተት ተሞክሯል?**

**ፕሮፌሰር መንግስቱ፡-** ከፆታ አኳያ ተንትነን አላየንም። ያየነው በኑሮ ደረጃ ነው። በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉት ይጎዳሉ። በአጠቃላይ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ በጣም እየተጎዱ ነው። ገቢያቸው ሌላ ወጪ መሸፈን ቀርቶ የምግብ ወጪ አይሸፍንላቸውም። በሌላ ሀገር የሚስተዋለው እኛ ሀገር እየተስተዋለ አይደለም፤ ህዝብ ታጋሽ ነው። መፍትሄ ይመጣል በሚል በትዕግስት የሚጠብቅ ህዝብ ነው ያለው።

**አዲስ ዘመን፡- የጎረቤት ሀገራት ቀጣናዊ ትስስርና የኢኮኖሚ አቅማቸው የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በመደገፍ ረገድ እንዴት ይመለከቱታል?**

**ፕሮፌሰር መንግስቱ፡-** መጠነኛ መደጋገፍ አለ። ነገር ግን ወደ ውጭ የሚልኩት ተመሳሳይ ምርቶችን ነው። ከእነርሱ የሚገባ ቢኖርም በቂ አይደለም። በዚያ ላይ ተመስርተን ኢኮኖሚያችን ማስቀጠል ይከብዳል፤ ግን እንደአማራጭ መጠቀም ይቻላል። ከውጭ የምናስገባቸውን በበቂ ደረጃ ከጎረቤት ሀገራት ማግኘት ከባድ ነው። ነገር ግን ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ኃይል በሚገባ ሲያመነጭ ወደ ውጭ የመላክ ዕድላችን ሰፊ ይሆናል።

በሌላ በኩል ከውጭ የሚገቡትን ምርቶች ለመተካት በትጋት መሥራት ይጠበቅብናል። ለምሳሌ የአፈር ማዳበሪያ መቶ በመቶ የሚገባው ከውጭ ነው። በዚህ ላይ ማተኮር አለብን። የቅባት እህሎችን ወደ ውጭ ከመላክ ይልቅ ሀገር ውስጥ ያሉ ፋብሪካዎች ዘይት በበቂ ደረጃ ማምረት አለባቸው። ይህን ማድረግ ከተቻለ የተመረተውን ዘይት ወደ ውጭ መላክ የበለጠ ገቢ ያስገኛል። በተቻለ መጠን በዚህ ዘርፍ ራስን ለመቻል ርብርብ ማድረግ ይገባል። በርካታ የሀገራችን ክፍሎች የቅባት አህል አምራች በመሆናቸው በዘይት ምርት ራሳችንን ችለን ወደ ጎረቤት ሀገራት የመላክ ዕድላችን ሰፊ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መታወክ የጀመረው መቼ ነው?**

**ፕሮፌሰር መንግስቱ፡-** ችግሩ መዋቅራዊ ነው። ቀደም ብሎ የጀመረ ነው። የተለያዩ ዘርፍ የሚባሉ አሉ። የግብርናው እና ኢንዱስትሪ ዘርፍ አምርተው ምርታቸውን ማቅረብ ላይ ገና ናቸው። እነዚህ ነገሮች የመቀነስ አዝማሚያ እያሳዩ ነው። እኛ ሀገር አገልግሎት ዘርፍ እየጨመረ ነው። የአገልግሎት ዘርፍ ጨመረ ማለት ፍላጎት ይጨምራል እንጂ ምርታማነት አይጨምርም። ይህ ጤናማነት አይደለም። በቅርብ ዓመታት ደግሞ ብሶበታል። በሀገር ውስጥ በነበረው ጦርነት፣ በራሺያ እና ዩክሬን ጦርነት፣ በኮረና እና ሌሎች ምክንያቶች የተነሳ ብሶበታል።

**አዲስ ዘመን፡-የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ አሶሼሽን በዓመት ምን ያክል ጥናት ያካሂዳል?**

**ፕሮፌሰር መንግስቱ፡-** በአማካይ በዓመት

**እኛ ሀገር አገልግሎት ዘርፍ እየጨመረ ነው። የአገልግሎት ዘርፍ ጨመረ ማለት ፍላጎት ይጨምራል እንጂ ምርታማነት አይጨምርም። ይህ ጤናማነት አይደለም**

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተጠየቅ

እስከ 15 ጥናቶችን ያካሂዳል። እስካሁን ያሉት ጥናቶች ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ሰጥተናል። በዚህ ዓመት ጠቅላይ ሚኒስትር ፅህፈት ቤትን ጨምሮ ለ10 የመንግሥት ተቋማት ተጠይቀን ሰጥተናል። በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ድርድር ላይ እና በሦስት ሀገራት ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ በተለይም በግድቡ ድርድር ላይ ኢትዮጵያ ምን ይዛ መቅረብ አለባት የሚለውንም አጥንተን አቅርበናል። ስደት ላይ እንዲሁም የኮረና ቫይረስ ወረርሽኝ የሚያስከትለው ተጽዕኖ እና መደረግ ስለሚገባው መፍትሄም ጥናት አዘጋጅተን አቅርበናል። በተጨማሪም በዋጋ ግሽበት ላይም ጥናቶችን አቅርበናል።

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ አሶሼሽን ስሀገሪቱ ኢኮኖሚ ዕድገት የከፋ ማነቆ ይሆናል በሚል እንደ ሥጋት የሚመለከተው ነገር አለ?**

**ፕሮፌሰር መንግስቱ፡-** አዎ! ስጋቱ ጦርነቱ ነው። ይህ ጦርነት የሚቀጥል ከሆነ እና እዚህም እዚያም ግጭቱ የሚቀጥል ከሆነ ኢኮኖሚው ወደ ጤንነት ይመለሳል ብለን አናምንም። ምክንያቱም ጦርነት ባለበት ቦታ ምርት ይቆማል። የተመረተም ቢኖር ስርጭቱ ላይ ችግር ይኖራል። ስለዚህ ይህ በዋጋ ንረት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ይኖረዋል። የሰው ሕይወትም ሆነ ንብረት ውድመትም በተመሳሳይ ሁኔታ አደጋ ይገጥመዋል። ትልቁ ተግዳሮት ጦርነት ነው። ስለዚህ ከጦርነቱ ጋር ተያይዞም ከሀገራት ጋር ያለን ግንኙነት ሌላው ነው። አንዳንድ ሀገራት ከጦርነቱ ጋር ተያይዞ ሀገሪቱ ላይ ጫና እየፈጠሩ ነው። በመሆኑም ግጭቱ ትልቅ ፈተና ይሆናል ብለን እናስባለን።

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ የህዝብ ብዛት መጨመር ኢኮኖሚው ላይ ጫና አይኖረውም?**

**ፕሮፌሰር መንግስቱ፡-** ከህዝብ ብዛት ጋር በተያያዘ ጥናት አካሂደናል። የህዝብ ቁጥር መጨመር በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ኢኮኖሚው ላይ ትልቅ ተጽዕኖ ስላለው በዚህ ላይ ትልቅ ሥራ መሠራት አለበት። የሥነ-ህዝብ ፖሊሲም መጠናት አለበት ብለናል። ሀገሪቱ ያላት የሥነ-ህዝብ ፖሊሲ ከ30 ዓመት በፊት የነበረው ነው። በመሆኑም አዲስ ፖሊሲ መውጣት አለበት። ነገር ግን ህዝብ መቀነስ ብቻ ውጤታማ አያደርግም። አሁን ባለው ህዝብ ምርታማነትን መጨመር ይቻላል። በዓመት ሁለት እና ሦስት ጊዜ ማረስ ይቻላል።

የህዝብ ቁጥር መጨመር እንደ ጥሩ አጋጣሚ መውሰድ ይቻላል። ቻይናን እንደ አብነት ብንወስድ የአንድ ልጅ የመውለድ ፖሊሲ አወጣች። በመቀጠል ሁለት ልጅ መውለድ ይቻላል የሚል ፖሊሲ አወጣች። በመቀጠል ደግሞ ሙሉ ለሙሉ አነሳችው። ይህ የሆነው ህዝባቸውን ምርታማ በማድረጋቸው ነው። በመሆኑም የህዝብ ቁጥርን መቀነስ ብቻውን ግብ አይደለም። ጎን ለጎን ምርታማነት ላይ መሥራት ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- ስዋጋ ግሸበት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?**

**ፕሮፌሰር መንግስቱ፡-** የዋጋ ግሽበት የሀገራችን የወቅቱ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው፡ የተፈጠረው የኑሮ ውድነት የህብረተሰቡን ህልውና እየተፈታተነ ይገኛል። የሁሉንም ህብረተሰብ ክፍል የመግዛት አቅም የሚቀንስ ሲሆን የድሃ ድሃ የሆኑትን ዜጎች ክፉኛ እየጎዳ ይገኛል። የዋጋ ግሽበት በጠባቡ ሲተረጎም በኢኮኖሚው ውስጥ የገንዘብ ፍሰት ሲበዛና የሚገዛው ዕቃ እና አገልግሎት ሲያንስ የሚፈጠር ክስተት ነው። ሲተነተን ግን በውስጡ ውስብስብ በሆኑ፤ የተሳሰሩ ኢኮኖሚያዊ የሆኑ እና ኮኖሚያዊ ያልሆኑ ጉዳዮችን የያዘ ነው ለምሳሌ፤ የኢኮኖሚ አስተዳደር (governance) በተመለከተ ኢኮኖሚውን መቆጣጠሪያ የህግ ማዕቀፎች መጥበቅና መላላት፤ የንግድ ህጎች፤ የመንግሥት መዋቅር ክፍተት አስተዋጽኦ አላቸው።

የምርት ገበያ በተመለከተ የግብዓት ዋጋ፣ ቀረጥና ግብር፣ የኢኮኖሚ ድጎማ (subsidy)፤ የግብይት ሰንሰለትና መዋቅር (marketing chain and structure) ይገኙበታል። የፋይናንስ ገበያ በተመለከተ የብድር አቅርቦት፤ የወለድ መጠን፤ የውጭ ምንዛሪ፣ እና የገንዘብ አቅርቦት ይገኙበታል። እነዚህን በሁለት ዋና ዋና ጎራዎች ከፍሎ ማየት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- የአቅርቦት ምንጮች እንዴት ይገኛሉ። የአቅርቦት ማነስ ከምን ይመነጫል?**

**ፕሮፌሰር መንግስቱ፡-** አቅርቦት ከሁለት ምንጮች ይገኛሉ። ሀገራዊ ምርት እና ገቢ ንግድ (imports) ላይ ነው። የነፍስ ወከፍ የምግብ እህሎች ምርት መቀነስ ለዋጋ

**የግብርና ምርታማነትን የሚያፋጥኑ የአሰራር ዘዴዎችን ለአነስተኛ አርሶ አደሮች ማቅረብ፤ የገቢ ንግድ ላይ የሚጣለው ታሪፍ ተመጣጣኝ የሚሆንበትን መንገድ መፈለግ፤ ከተቀማጭ ገንዘብ የሚሰጠው ወለድና ከብድር የሚጠየቀው ገንዘብ የዋጋ ግሽበትን ያገናዘበ እንዲሆን ማድረግ ሊወሰዱ ከሚችሉ እርምጃዎች ጥቂቶቹ ናቸው**

ግሽበት ከፍተኛ ድርሻ አበርክቷል። በ1990 ዎቹ አንድ ኩንታል ምርት በነፍስ ወከፍ የነበረው ዕድገት እያሳየ መጥቶ እ.ኤ.አ በ2016 ዓ.ም 2ነጥብ65 ኩንታል ደርሶ ነበር። ሆኖም ግን ከ2016 በኋላ ማሽቆልቆል ጀምሯል። የጥራጥሬ እህሎች ምርትም እንዲሁ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ በመቀነስ ላይ ሲሆን፤ የቅባት እህሎች ምርት አነስተኛ ቢሆንም የተረጋጋ ምርት እንዳለ መረጃዎች ያሳያሉ። የአትክልት የነፍስ ወከፍ ምርት ዕድገት ለብዙ ዓመታት ከአንድ ኩንታል በታች ነበር። በ2005 አንድ ኩንታል ደርሶ በመቀጠልም 2012 ላይ ደግሞ 1ነጥብ5 ኩንታል ከደረሰ በኋላ በማሽቆልቆል ላይ ይገኛል። በሌላ በኩል ፍራፍሬ በመጠኑም ቢሆን መሻሻል በማሳየት በነፍስ ወከፍ አንድ ኩንታል ደርሷል።

የሥጋ ምርት ዕድገት ባለፉት በርካታ ዓመታት ከፍተኛ መዋዠቅ የታየበት ነው። እ.ኤ.አ በ2010 ላይ 8ነጥብ5 ኪሎ ግራም ደርሶ አሁን ሰባት ኪሎ ግራም ገደማ ነው። ለህጻናት ከፍተኛ አልሚ የሆነው የወተት ምርት እስከ 2010 እየዋዠቀም ቢሆን የመጨመር ሂደት ነበረው። እ.ኤ.አ ከ2010 በኋላ ከፍተኛ ማሽቆልቆል ላይ ይገኛል።

የእንቁላል ምርት ከሁሉም ምርቶች በበለጠ የመዋዠቅ ባህሪ የሚያሳይ መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል። አጠቃላይ የኢንዱስትሪ ምርት በነፍስ ወከፍ ዕድገት በተከታታይ እስከ 2010 ሲጨምር ቆይቶ እ.ኤ.አ ከ2016 በኋላ ማሽቆልቆል ላይ ይገኛል። ሦስቱን የኢኮኖሚ ዘርፎች ስንመለከት ከአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት ሲነጻጸሩ ግብርናው እ.ኤ.አ በ1990ዎቹ ከነበረበት 60 ከመቶ በግማሽ ወርዶ ይታያል።

የኢንዱስትሪው ድርሻ ከ10 ከመቶ በታች ከነበረበት ወደ 30 ከመቶ እየተጠጋ ይገኛል። በሌላ በኩል የአገልግሎት ዘርፍ ከነበረበት 30 ከመቶ ወደ 40 ከመቶ ዕድገት አሳይቷል። ይህ ዘርፍ የመሪነት ደረጃ መያዝ የሚያመለክተው ኢኮኖሚው መዋቅራዊ ችግር እንዳለበት የሚጠቁም ነው።

የአቅርቦት ዕድገት በዋጋ ግሽበት ላይ ያለውን ተጽዕኖ ስንመለከት የግብርና አጠቃላይ ምርት ማደግ ሌሎች ጉዳዮች እንዳሉ ሆነው የገበያ ዋጋውን የማረጋጋት ባህሪ አለው። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የኢንዱስትሪ ምርትና እና የአገልግሎት ዘርፍ ማደግ የዋጋ ግሽበትን እንደሚያባብስ መረጃዎች ያሳያሉ።

**አዲስ ዘመን፡- የሀገሪቱ የንግድ ሚዛንስ እንዴት ይታያል?**

**ፕሮፌሰር መንግስቱ፡-** የገቢ ንግድን በተመለከተ እስከ 2016 በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ ወጥቶ 20 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ደርሶ ነበር። በአሁኑ ወቅት 18 ሚሊዮን ገደማ ይገኛል። ከአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት ጋር ሲታይ ግን እ.ኤ.አ በ2010 ከነበረበት 30 በመቶ፣ በ2020 ወደ 17 ከመቶ ዝቅ ብሏል። ይህም ኢትዮጵያን ከአፍሪካ ዝቅተኛ ገቢ ንግድ ተሳታፊ አራት ሀገራት አንዷ ያደርጋታል።

የወጪና ገቢ ንግድ ግብይት የሚካሄደው በውጭ ምንዛሪ እንደሆነ የምንዛሪው ውጣ ውረድ የዋጋ ግሽበት ላይ ተጽዕኖ እንደሚኖረው ይታወቃል። እስከ 1990 ዎቹ መጀመሪያ ቋሚ የነበረው የምንዛሪ ዋጋ በመጠኑም ቢሆን በገበያ እንዲወሰን ተደርጓል። በመሆኑም የአንድ የአሜሪካ ዶላር ዋጋ ከነበረበት 2ነጥብ07 ብር አሁን ከ50 ብር በላይ ደርሷል። ምንም እንኳ ቀደም ሲል የነበረው የብር ጥንካሬ የኢኮኖሚውን ጥንካሬ ባያመለክትም፤ አሁን ባለው ፍጥነት የብር ዋጋ ማሽቆልቆሉ የዋጋ ግሽበቱን ካባባሱት ጉዳዮች አንዱ ሆኗል።

**አዲስ ዘመን፡- እንደ ሀገር ከውጭ ገቢ ምርቶች ላይ የሚጣለው ታሪፍ ተወዳዳሪ ያደርጋል?**

**ፕሮፌሰር መንግስቱ፡-** በወጪ እና በገቢ ንግድ ላይ የሚጣለው ታሪፍ መንግስት ገቢ እንደሚጨምር ይታመናል። ከዚህም ከፍተኛ ገቢ በመሰብሰብ ኢትዮጵያ ከ10 የአፍሪካ ሀገራት ሠባተኛ ስትሆን፤ ከፍተኛ የታሪፍ መጠን በመጣል አራተኛ ላይ ትገኛለች። መረጃው እንደሚያሳየው ከፍተኛ የታክስ ገቢ ዋጋ ግሽበትን ያባብሳል። የወጪ ንግድን በተመለከተ ኢትዮጵያ ዝቅተኛ ተሳታፊ ከሚባሉ 10 የአፍሪካ ሀገራት ሦስተኛ ነች። የወጪ ንግድ እያደገ ሲመጣ የዋጋ ግሽበትን ሊያባብስ እንደሚችል ይታመናል። ይህን ማመጣጠን ከፍተኛ የፖሊሲ እሳቤ ይጠይቃል። በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ የሚከሰቱ ግጭቶች የአቅርቦት ሰንሰለቱን (supply chain) በማስተጓጎል የዋጋ ግሽበትን አባብሷል። ለምሳሌ በአሁኑ ወቅት እየተካሄደ ያለው የሩሲያ እና ዩክሬን ጦርነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከሁለቱ ሀገራት ጋር የንግድ ግንኙነት ያላቸውን ሀገራት ኢኮኖሚ የሦስት መሰረታዊ ዕቃዎች አቅርቦት ማለትም ምግብ፣ ነዳጅና ማዳበሪያ አውኳል። እንደ ኢትዮጵያ ያሉ በሦስቱም መሰረታዊ ዕቃዎች ራሳቸውን ያልቻሉ፤ የገበያ አማራጭና ክምችት የሌላቸው፤ ከግጭቱ በፊት በሌሎች ችግሮች የተወጠሩ ሀገራት ክፉኛ ተጎድተዋል።

**አዲስ ዘመን፡- በየጊዜው የፍላጎት መጨመር ኢኮኖሚያዊ እሳቤውና ትርጉሙ ምንድን ነው?**

**ፕሮፌሰር መንግስቱ፡-** የፍላጎት መጨመር ከላይ እንደተጠቀሰው የገንዘብ ፍሰት አለመመጣጠን የዋጋ ግሽበትን ያስከትላል። የገንዘብ ፍሰትን የሚያመጣጥነው ከተቀማጭ ገንዘብ የሚከፈለው ወለድና ከብድር የሚጠየቀው ወለድ ነው። ከተቀማጭ ከፍተኛ ወለድ ከተሰጠ ገንዘብ የማስቀመጥ ዝንባሌ ይጨምርና በኢኮኖሚው ውስጥ የገንዘብ ፍሰት ይቀንሳል። ወለዱ ዝቅተኛ ከሆነ ገንዘብ የማስቀመጥ ዝንባሌ ይቀንስና በኢኮኖሚው ውስጥ የገንዘብ ፍሰት ይጨምራል። ይህም የዋጋ ግሽበትን ያባብሳል። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ ለተቀማጭ (ቁጠባ) ዝቅተኛ ወለድ ከሚሰጡ 10 የአፍሪካ ሀገራት ስምንተኛ ደረጃ የያዘች መሆኑን መረጃው ያሳያል።

**አዲስ ዘመን፡-ከምግብ ፍጆታዎች ስዋጋ ግሸበት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉት ያሉት የትኞቹ ናቸው?**

**ፕሮፌሰር መንግስቱ፡-** ከግብርና ምርቶች የእህል ዋጋ እስከ 39 ከመቶ፤ የቁም ከብቶችና የእስሳት ተዋጽኦ 18 ከመቶ ድርሻ አላቸው። ቀጥታ ከምንመገባቸው ውስጥ ዳቦ 42 ከመቶ፤ አትክልትና ፍራፍሬ 19 ከመቶ ድርሻ አላቸው። ምግብ ነክ ካልሆኑት የቤት ኪራይ፤ ውሃ እና መብራት 35 ከመቶ፤ ህክምና፤ ትራንስፖርት፤ የቤት ዕቃ 13 ከመቶ፤ ልብስና ጫማ እንዲሁ 13 ከመቶ ድርሻ አላቸው። በመሆኑም ኢትዮጵያ ከፍተኛ የዋጋ ግሸበት ካላቸው 10 የአፍሪካ ሀገራት ዘጠነኛ ላይ ትገኛለች።

**አዲስ ዘመን፡-የኢትዮጵያን ኢኮኖሚክስ አሶሴሽን ስፖሊሲ አውጪዎች የሚሰጠው ምክር ሐሳብ ምንድን ነው?**

**ፕሮፌሰር መንግስቱ፡-** ተግዳሮቶች ለፖሊሲ እርምጃ መንደርደሪያ ናቸው። በመሆኑም የግብርና ምርታማነትን የሚያፋጥኑ የአሰራር ዘዴዎችን ለአነስተኛ አርሶ አደሮች ማቅረብ፤ የገቢ ንግድ ላይ የሚጣለው ታሪፍ ተመጣጣኝ የሚሆንበትን መንገድ መፈለግ፤ ከተቀማጭ ገንዘብ የሚሰጠው ወለድና ከብድር የሚጠየቀው ገንዘብ የዋጋ ግሽበትን ያገናዘበ እንዲሆን ማድረግ ሊወሰዱ ከሚችሉ እርምጃዎች ጥቂቶቹ ናቸው። በመንግሥት አካላትና በማህበረሰቡ ዘንድ የሚታዩ ብክነቶች ማስወገድ፤ የኃይል አጠቃቀም ማሻሻልና በዋጋ ግሽበቱ በከፍተኛ ደረጃ የሚጠቁ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለይቶ መደገፍ ያስፈልጋል። የዓለም አቀፍም ሆነ ሀገራዊ ሠላምና መረጋጋት ማስፈን፤ የአቅርቦት ሰንሰለቱን ስለሚያሳልጠው የዋጋ ግሽበቱን ይቀንሳል፤ ቢያንስ ዋጋውን የማረጋጋት ሚና ይኖረዋል።

እነዚህ የፖሊሲ እርምጃዎችን ሥራ ላይ የማዋል ኃላፊነት የመንግሥት ቢሆንም ጉዳዩ በመንግሥት አቅም ብቻ የሚፈታ ባለመሆኑ መንግሥትን ሊያግዝ የሚችል ነፃ የሆነ የአቅርቦትና ዋጋ ማረጋጊያ ቦርድ (Supply and Price Stabilization Board) ቢቋቋም ጠቃሚ ይሆናል። ይህ ቦርድም ከሚያከናውናቸው ተግባራት ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል። የሀገር ምርትና የገቢ ንግድ አቅርቦት አስተዳደር (ሚዛን ማስጠበቅ)፤ የዋጋን ማረጋጋት ካልሆነም የዋጋ ግሽበትን ግብ ማስቀመጥና ከዚያ እንዳያልፍ መከታተል፤ የዋጋ ግሽበት በማህበረሰቡ ላይ በተለይም የድሃ ድሃ ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ የሚቀንሱ የፖሊሲ እርምጃዎችን ማቅረብ፤ የተለያዩ ሴክተሮችን ማስተባበር ላይ ትኩረት ሊሰጥ እንደሚገባ ምክረ-ሐሳብ ይሰጣል፡

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## “ፈራን!”፡- “ስለምን ፈራችሁ?” አትበሉን

**የፈራነውማ…**

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በአገሬ ወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ መቆዘምና መተከዝ ስጀምር የማላውቀው የፍርሃት ቆፈን እየጨመደደኝ በቃላት ልገልጸው የማልችለው ውስጣዊ ብርድ ሲያንዘፈዝፈኝ ይታወቀኛል። ይሄ ስሜት የጸሐፊው ብቻ አይመስለኝም። ቢሆን ደስታውን አልችለውም። ግን አይመስለኝም። አገሬና ሕዝቤም ድምጻቸውን በጋራ አስተባብረው፡- “ፍርሃቱን የአንተ ብቻ ማን አደረገው? ቁዘማውንም ቢሆን ጠቅልለህ ለራስህ ብቻ አትውሰድ። እኛም እኮ በፍርሃት እንቅጥቅጥ እየተናጥን ነው፡፡” እያሉ የሚገስጹኝ እየመሰለኝ የራሴን ጥላ እስከ መፍራት እደርሳለሁ፡፡

“አስፈራኝ!” ያልኩትን ስሜቴን በሚገባ የሚገልጽልኝን በይዘቱ ጠነን፣ በርዝመቱ ዘለግ ካለው ከሎሬት ጸጋዬ ገ/መድኅን ተወዳጅ ግጥሞች መካከል ጥቂት የግጥም ስንኞችን በመዋስ ብእሬ ራሱ እንዳይፈራ በማበረታት ጭምር “ጉልበቴ በርታ! በርታ!” እያልኩ ከጋራ ስጋቶቻችን መካከል በአንዱ ላይ ቁዘማዬን እንቀጥላለን፡፡

**“ፍቅርን ፈራን፤ መቀራረብን ፈራን፣**
**እንዳልተዛመድን፤ እንዳልተዋደድን፣**
**ፈርተን መዋደድን፤ ጉርብትናን ናድን፡፡**
**ፍቅርን ፈራን፣ ጥላቻን ሰራን፣ ብቸኝነት ጠራን፣**
**በጋራ ቤታችን አጥር ድንበር ሰራን፡፡**
**መቻቻልን ነቀን፤ ስፀብ ተሟሟቅን፣**
**ስአመጽ ስንነሳ፤ ስሰላም ወደቅን፣**
**አገር ስትቃጠል ከዳር ሆነን ሞቅን፡፡**
**መወያየት ጠላን፤ መነጋገር ጠላን፣**
**መደማመጥ ጠፍቶ፤ መነቋቆር በዝቶ፣**
**መናናቅ በርክቶ፡፡**
**የተስፋ ሻማችን ተለኩሶ፣**
**ወጋገኑ መታዬት ሲጀምር አድማሱን ጥሶ፣**
**እኛ ግን ራቅን፤ ብሩኅ ነገን ራቅን፣**
**ዛሬን በመጣበቅ ትናንትን ናፈቅን፡፡**

ይለናል ጠቢቡ ብእረኛችን። እንኳንም በዛሬው ቀናችን አልኖርክ ጋሼ!

**እባብ ያየ በልጥ በረየ፤**

ሰሞኑን ከሃይማኖት ጋር ተያይዘው በተፈጠሩ ሁከቶች፣ ሞቶችና የንብረት ውድመቶች ምክንያት ምዕመናን እንደየእምነታቸው በየደጀ ሰላማቸው አደባባዮች ላይ ተደፍተው እምባቸውን እያጎረፉ ፈጣሪን በመሞገት ላይ ናቸው። የየሃይማኖቶቹ “አበ ነፍሶችም” “መንጎቻቸውን” ከጠብና ከጥፋት ለመታደግ ከቅዱሳት መጻሕፍታቸው ላይ እየጠቀሱ ምክርም ውግዘትም እያሰሙ ነው፡፡

ፖለቲከኞችም አርፈው አልተቀመጡም፤ በይደር የተላለፈው የትናንቱ ዳፋ ወደ ዛሬ ጀምበር ዞሮ አገር እያተረማመሰ መሆኑን ደጋግመው በመግለጥ ናላቸው መዞሩን እየገለጹልን ነው። ከየስብሰባቸው መድረኮች በሚወጡት መግለጫዎችም እኩይ የሚሉትን የጥፋት ኃይል መልሰው መላልሰው በንግግር እየወቀጡ በልብ ስፋት እንድንታገስ እየመከሩን ነው። የአገር አውራ ሽማግሌዎችና እናቶችም በእንብርክክ ተደፍተውም ሆነ በጥበብ ቃል እያግባቡ አጥፊና ጠፊውን ለማቀራረብና እርቅ ለማውረድ በትጋት እየሰሩ እንደሆነ በየሚዲያዎቹ የዜና ሰዓት ብቅ እያሉ ተስፋ እንዳንቆርጥ እያበረታቱ ይመክሩናል።

የጸጥታ ክፍሎችም ጉዳዩ ከቁጥጥራቸው ውጭ ያለመውጣቱን አስረግጠው ቢነግሩንም የፈራነውና የተፈራራንበት “በላ” ግን እየተደጋገመ በፍርሃት ስለሚያንዘረዝረን “ፈራን!” ብለን ብንበረግግ አይፈረድብንም። ለምን ቢሉ “እባብ ያየ በልጥ በረየ” [በረየ፡- ፈራ፣ ደነገጠ፣ ሸሸ፣ በረገገ፣ ፈረጠጠ፣ ወገሸ ወዘተ.] እንዲል ብሂላችን “ብዙ መሰል ተናዳፊ አገራዊ እባቦች በታሪካችን ውስጥ ደጋግመው ሲነድፉን ስለኖሩ በልጥ በሚመስሉት ወቅታዊ ፈተናዎቻችን” ብንበረይ አንወቀስም።

**ታሪካችንን ስላላከበርነው አኩርፎን ይሆን?**

ኢትዮጵያ የዛሬዎቹን ታላላቅ ሃይማኖቶች “ቤት ለእንግዳ” ብላ ልቧን ከፍታ፣ እጆቿን ዘርግታ፣ በፍቅርና “በአንቱታ” ዝቅ በማለት አክብራ መቀበል ከጀመረች ሺህ ዓመታት ተቆጥረዋል። የአይሁድ እምነት ወደ አገራችን የገባው የእምነቱን ቅዱሳት መጻሕፍት ይዞ ብቻም ሳይሆን በዘውድና በንግሥና ከብሮ ጭምር ነው። ከንግሥት ሳባና ከንጉሥ ሰሎሞን የተወለደውንና “ለሞዓ አንበሳ ዘእምነገድ ይሁዳ” የዘር ሐረግ በአባትነት የሚጠቀሰውን የቀዳማዊ ምኒልክን ሥርወ መንግሥት ማስታወሱ ብቻ በቂ ይሆናል።

ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ የዚሁ የሞአ አንበሳ 225ኛው ወራሴ ዙፋን እንደሆኑ ሲታመን መኖሩ ያልመሸበት ታሪካችን ነው። [ምንጭ፡- 1ኛ ነገሥት ምዕ. 10 እና በቅርቡ በደራሲ አምሳሉ መሐሪ ተጽፎ ለንባብ የበቃውን “ቤተ-እስራኤል ከትናንት እስከ ዛሬ” የሚለውን ግሩም መጽሐፍ እና “ዝክረ ነገር” የተባለውን ታላቅ ሰነድ ማመሳከር ይቻላል፡፡ ] “አፈ ታሪኩ በማስረጃ ከሚመሳከሩት ሰነዶች ጋር ይቃረናል” - እያሉ አንዳንድ ምሁራን ፀጉር እየሰነጠቁ የሚከራከሩባቸውን ዝንጉርጉር መሟገቻዎች ለጊዜው በዚህ ጽሑፍ ለመጠቃቀስ ዐውዱ ስለማይፈቅድ እናልፈዋለን፡፡

ከአይሁድ እምነት ቀጥሎ ወደ ኢትዮጵያ የገባው የክርስትና ሃይማኖትም ቢሆን ዕድሜው ሁለት ሺህ ዓመት ሊሞላው የቀሩት ጥቂት ዓመታት ብቻ ናቸው። የወንጌሉን የምሥራች ይዞ ከእየሩሳሌም ወደ አገሩ የተመለሰውን ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ፊሊጶስን እንደ የክርስትና እምነት ዋና መግቢያ ምክንያት አድርገን ከተስማማን ሁለት ሺህ ዓመት ዕድሜውን የሚደፍነው ከሁለት ዐሥርት ዓመታት በኋላ መሆኑን የሚያረጋግጥልን የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ምዕራፍ 8 ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ የተጻፉ በርካታ ማጣቀሻዎች እንዳሉም ማስታወሱ አግባብ ይሆናል፡፡

በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን (በ340 ዓ.ም ገደማ) ለመጀመሪያ ጊዜ አክሱም ላይ ወንጌል ሰብከው ክርስትናን ያስተዋወቁትን ግሪካዊውን ጳጳስ ፍሬምናጦስን (የክህነት ስማቸው ከሳቴ ብርሃን “ብርሃን ገላጭ”) ለኢትዮጵያ ክርስትና መነሻ እናድርግ ከተባለም የእምነቱን የዕድሜ ርዝመት እጅግም አይቀንሰውም። የኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች ታሪክ እድሜም ከአንድ ክፍለ ዘመን ተኩል በላይ ስለሆነ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም፡፡

የእስልምና እምነት ወደ ኢትዮጵያ አገባብ ታሪክም እንዲሁ በሰላምና በታላቅ አክብሮት የሚዘከር እንደሆነ ከታሪኩ መረዳት ይቻላል። በ615 ዓ.ም ነብዩ መሐመድ 15ቱን ተከታይ ሱሀባዎች ከወቅቱ የቁረሾች ስደት ዞር እንዲሉ የላኳቸው አፍቃሬ ሰላም ንጉሥ ወደ አለበት የሐበሻ አገር እንደሆነ ታሪኩ በዝርዝር ይነግረናል። የዚህ ጽሑፍ አቅራቢም ከጥቂት ዓመታት በፊት ትግራይ ውስጥ በሚገኘው በጥንታዊው አልነጃሺ መስጊድ ለጉብኝት በተገኘበት ወቅት የ15ቱ ሱሀባዎች አጽም በክብር አርፎበታል የሚባለውን የመስጊዱን የውስጠኛ ክፍል ለመጎብኘት ዕድል ገጥሞት ነበር፡፡

ይህን የመሰለ ደማቅ፣ ሰላማዊና ፍቅር የተሞላበትንና በሺህ ዘመናት ውስጥ ሃይማኖቶችን በእኩልነት የመቀበል ታሪክ ባለቤት ነች በምትባለዋ ኢትዮጵያችን ውስጥ “የፍቅር ወንጌል” የሚባለው ቅዱስ መጽሐፍ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እየተሰበከ ኖሮ፣ “የሰላም መሠረት ነው” የሚባለው የእስልምና እምነትም እንዲሁ የተመሠረተበት ቅዱስ ቁርዓንም እንዲሁ ለሺህ ዘመናት ሲቀራ ኖሮ” ምን ሆነንና ምን ቢነካን ነው አፍቃሬ ሃይማኖተኝነትን እንደ ሽፋን እየቆጠርን የምንገዳደለው? አደብ ገዝተን የኅሊናችንን ወቀሳ ብናደምጥ ምክንያቱ በሚገባ ይገለጽልናል።

በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች እየተደመጡና እየተስተዋሉ ያሉ እጅግ አሳዛኝና ዘግናኝ ድርጊቶች ምንጫቸውና መነሻቸው ግራ እስኪያጋባን ድረስ መስጊዶች ተቃጠሉ፣ አብያተ ክርስቲያናት የዶግ ዐመድ ሆኑ፣ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ተገዳደሉ ወዘተ. የሚለው መርዶ ከቀን ወደ ቀን ፍርሃትና ስጋት ላይ ጥሎን ብንቆዝም፣ ብንብከነከን፣ ብንበረግግና ብንበረይ “ለምን ፈራችሁ?” ተብለን ልንጠየቅና ልንወቀስ በፍጹም አይገባም፡፡

ሃይማኖታዊ ምልከታችንን ትንሽ ከፍ አድርገን እናግዝፈውና የወንጌሉ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን አገራዊ መከራችንን ሲመለከትና ሲያስተውል ስሙን የተሸከሙትን “ክርስቲያኖች ነን ባዮችን” በርግጥ ልጆቼ ብሎ ይጠራቸዋል? አይመስለንም። “በሰላም አስተምህሮው” መታወቂያነት የሚገለጸው “እስልምና” ስሙ በክፉ እየተነሳ በዛኛውም ሃይማኖት ሆነ በዚህኛውም ገዳይ ሲፎከርበት፣ ሟች የደም ግብር ሲከፍልበትስ የነብዩ መሐመድ መንፈስ ምን እያለ ይወቅሰን ይሆን? ዐይኖቹ ሁሉ በምድር ላይ የጸኑት ቅዱሱ የሰው ልጆችና የፍጥረታት ሁሉ ገዢው ጌታ አምላክስ እንደምን ያዝንብን፤ ፊቱንም ያጠቁርብን፣ በፍርዱም እንደምን አይጨክንብን?

ከየትኛውም የሃይማኖት ወገን በግፍ የተገደሉት የንጹሐን ነፍሳትስ ወደ ፈጣሪ ዘንድ ሲደርሱ ስለተፈጸመባቸው የግፍ አገዳደል ቢፈረጅ ጌታ ፊት የሚመሰክሩት ምን እያሉ ይሆን? የጌታችን ስም ሲታወስባቸውና ጸሎታችን ወደ ላይ ሲያርግባቸው የሚውሉት አብያተ ክርስቲያናትና መስጂዶች በእሳት ጋዩ፣ በአመጻኞች እጆች ወደሙ መባል፤ እንኳን ለፈጣሪ ቀርቶ ለሰው ኅሊናስ ይመቻል? ፈራን ያሰኘን፣ ውስጣችንን ብርድ ብርድ ብሎ ያንቀጠቀጠን ክፉ ፍርሃትና መከራ ምክንያቱ ይህ ነው፡፡

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በዘመነ ደርግ የነበረውን የሃይማኖት ስደትና የአማኞችን የመከራና የግፍ ዓይነት ተንትኖ ባቀረበበት “ኤሎሄና ሃሌሉያ - 1992 ዓ.ም” በሚለው ዳጎስ ያለ መጽሐፉ ውስጥ በጨካኙና በእምነት የለሹ የደርግ መንግስት ፖሊሲ መሠረት በሺህዎች የሚቆጠሩ የጸሎት ቤቶች እንደተቃጠሉ፣ እጅግ በርካታ ምዕመናን ለሞት፣ ለአካላዊ ጉዳትና ለኅሊናዊ ስብራት እንደተዳረጉ በበቂ ማስረጃ አስደግፎ መረጃዎቹን ለኅትመት አብቅቷል። ይህንኑ አስጨናቂ የወታደራዊ አገዛዝ በመሸሽም እውቀትና አቅም የነበራቸው በርካታ ኢትዮጵያዊያን ከአገር ወጥተው እንደኮበለሉ ጭምር ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

ይህ ጸሐፊ ራሱም ቢሆን የመከራው ተካፋይ ስለነበር ጥናቱ የሚያካትተው የራሱንም ተሞክሮ በማሳየት ጭምር ነው። “ሥጋ ያንገፈገፈው ሰው ቀይ በሬ ሲያይ ይሸሻል” እንዲሉ፤ ጸሐፊው “ፈራን!” እያለ ጭንቀቱን የገለጸው ከሃይማኖት ጋር የተቆራኘ ይህንን መሰል ክፉ ትዝታ ስላለውና ትዝታው ደግሞ የደም ግብር ጭምር የተከፈለበት፣ የዜግነት መብቱ የተገፈፈበትና በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገራት ጭምር የትምህርት ዕድል እንዳያገኝ በግፍና በግፈኞች የተፈረደበት ስለነበር “እባብ ስላየ በልጥ ቢበረይ” ፍርሃቱ ሊጋነን አይገባውም፡፡

ዛሬ በጀብደኝነትና “የቀናኢ ሃይማኖትን ካባ በመደረብ” የሚፈጸሙ ድርጊቶች በሙሉ ነገ ዋጋ የሚያስከፍሉት “ተጠያቂ መሆን የሚገባቸው እነ እከሌ ናቸው” እየተባለ ጣት የሚቀሰርባቸውን ብቻ ሳይሆን ራስና የራስ የሆኑት ጭምር በምድራዊም ሆነ በሰማያዊ የፍትሕ ወንበር ፊት እንደሚቆሙ ሊታወቅ ይገባል። ትናንት ደም የተቃባንበት የእርስ በእርስ የጦርነት ጠባሳ ሳይጠግግና አገራዊ የሀዘን ማቃችንን ሳንለውጥ ይህም አነሰ ተብሎ በሃይማኖት ስም የሚፈጸሙ እኩይ ድርጊቶች ከወዲሁ ተገቢው እርምጃ ካልተወሰደባቸው በስተቀር ውሎ አድሮ መከራችንን ቧጠን ወደማንወጣበት አዘቅት መደፈቃቸው አይቀርም፡፡

መንግሥት ሆይ! “በትረ መኮንንህን” ወደ በትረ ፍትሕ ለውጠው። የሃይማኖት አባቶች ሆይ! በመንጋ መሃል ሆነው እንደሚበጠብጡ ኮርማዎች ምእመኖቻችሁን “ጃስ!” እያሉ ወደ ጥፋት የሚመሩትን “ፀረ ሰላም ተዋንያንን” አንድም በምክር አለያም በውግዘት አደብ አስገዙልን። የማሕበረሰቡ የሽበት ባለፀጋዎች ሆይ! ሽበታችሁን ወደ ሺህ ውበት ለውጣችሁ ለጥፋት የሚያገነግኑትን በምክር ቃል ወደ ኅሊናቸው መልሱልን። ያኔ ፍርሃታችን ተገፎ በአገራችን ተዘልለን እንኖራለን።

ጉልበታቸውን በሴራና በሸር ላደነደኑ፣ በአንደበታቸው ቅዱስ መጻሕፍትን እያጣቀሱ በተግባራቸው ግን የሞት ቀስት ለሚያስወነጭፉ “የደም ባለዕዳዎች” እባካችሁ ወደ ቀልብያችሁ ተመለሱ። በምድር ቆይታችሁ በፀፀት፣ በሰማይ ቤታችሁ በሲኦል ከመሰቃየት ዛሬ በንሰሃና በመመለስ ለሥጋችሁ እረፍትን ለመንፈሳችሁም እርካታን ምረጡ የመልእክቱ ማጠቃለያ ነው። ቀሪውን ጉዳይ ለመንግሥት እንተዋለን። ሰላም ይሁን!

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

## የአገር ባህል አልባሳት ዋጋ - በሽሮ ሜዳ ገበያ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ኢትዮጵያ ካላት በርካታ መንፈሳዊና ቁሳዊ ባህሎች መካከል የአገር ባህል አልባሳቶቿ አንዱ ነው። በተለይም አሁን አሁን በተለምዶ የሀበሻ ልብስ ተብሎ የሚታወቀውና በብዛት በባህላት ወቅት የሚለበሰው የአገር ባህል አልባሳት መልክና ዲዛይኑን እየቀያየረ በአዘቦትም ፋሽን ሆኖ እየተለበሰ ይገኛል። ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች መገኛ አገር እንደመሆኗም እያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ የየባህሉን አልባሳት በመልበስ አካባቢውን ያስተዋውቃል፡፡

ማህበረሰቡ በአገር ባህል አልባሳት ከመዋብና ከመድመቅ ባለፈ ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች መገኛ፣ የተለያዩ ባህላዊና መንፈሳዊ ባህሎች ባለቤት፤ ስለመሆኗም ለውጭው ዓለም እያስተዋወቀበት ይገኛል። ብዙዎች የሚያጌጡበትና የሚዋቡበት የአገር ባህል አልባሳት በተለይም በሰርግና በባእላት ወቅት በብዛት ተዘውትሮ ይለበስ እንጂ በዘርፉ ባለሙያዎች አማካኝነት ከሰርግና ከባዕላት ወቅት ባለፈም መለበስ እንዲችል በተለያዩ ዲዛይኖች እያመረቱት ይገኛሉ።

አሁን አሁን ታዲያ ሸማኔው የተጠበበት የጥበብ ሥራ በቀላሉ ማህበረሰቡ ጋር ለመድረስ የዋጋው ሁኔታ እጅጉን ፈታኝ ያደረገው ስለመሆኑ ይነገራል። እርግጥ ነው ከምግብ ሸቀጣ ሸቀጥ ቀጥሎ ከፍተኛ የዋጋ ንረት እየታየበት ያለው አልባሳት ነው። በተለይም በውጭ ምንዛሪ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ አልባሳትና የምግብ ሸቀጣሸቀጦች ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት እየታየባቸው ያሉ ቢሆንም የአገር ባህል አልባሳትም በተለያዩ ምክንያቶች ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ አሳይተዋል። በዛሬው የንግድና ግብይት ገጻችንም የሽሮ ሜዳ አገር ባህል ገበያው ምን እንደሚመስል በመቃኘት ሸማችና ነጋዴውን በማነጋገር እንደሚከተለው አቅርበናል።

የሸማኔው የእጅ ሥራዎች በስፋት ከሚስተዋሉበትና የጥበብ ባህር ከሚመስለው ሽሮ ሜዳ የአገር ባህል አልባሳት ለመግዛት ወዲህ ወዲያ ሲሉ ያገኘናቸው ሸማች ወቅቱ የፋሲካ በዓልና የሰርግ ጊዜ እንደመሆኑ አልባሳቱ በእጅጉ ይፈለጋል፤ ሆኖም ግን ዋጋው የሚቀመስ አልሆነም በማለት ሀሳባቸውን ያካፈሉን ወይዘሮ አልማዝ በቀለ ናቸው። እንደሳቸው ገለጻ የአገር ባህል አልባሳት በተለይም በባዕላት እና በሰርግ ወቅት በእጅጉ የሚፈለግ መሆኑን ገልጸው፤ በአሁኑ ወቅት ግን ዋጋው እጅጉን መወደዱን ይገልጻሉ፡፡

የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ በዓል የሆነው የፋሲካ በዓልን ተከትሎ የተለያዩ ፕሮግራሞችና ሰርጎች ይከናወናሉ። ለዚህም በአብዛኛው የአገር ባህል አልባሳት ይፈለጋል የሚሉት ወይዘሮ አልማዝ፤ እርሳቸውም ሰርግ ኖሮባቸው ለመግዛት እንደፈለጉ ጠቁመው፤ ነገር ግን ዋጋው የሚቻል እንዳልሆነ ነው ያጫወቱን። የአገር ባህል በአገር ውስጥ የሚመረት ሆኖ ይህን ያህል መወደዱ ሰዎች በአገራቸው ምርት እንዳይኮሩና እንዳይለብሱ ያደርጋቸዋልም ብለዋል፡፡

ዋጋው እጅጉን ውድ ይሁን እንጂ ሸማኔው የሚሰራቸው የእጅ ሥራ ጥበቦች ግን ተወዳዳሪ የሌላቸውና እጅጉን ውብና ድንቅ ስለመሆናቸው ያነሳሉ ወይዘሮ አልማዝ። በየጊዜው እጅጉን የተዋቡና የሚደነቁ የተለያዩ የጥበብ ሥራዎች የሚታዩ ስለመሆናቸው በመጥቀስ የሸማኔውን የጥበብ ሥራ አድንቀዋል። ታድያ እንዲህ ያማረና የተዋበውን ጥበብ ማንኛውም ማህበረሰብ ገዝቶ መልበስ ቢፈልግም ዋጋው ግን የማህበረሰቡን የመግዛት አቅም እጅጉን እየተፈታተነው ይገኛል። ወደፊትም ዋጋው በዚሁ ከቀጠለ የአገር ባህል ገዝቶ መልበስ የሚቻል አይሆንም ብለዋል፡፡

ሰዎች በአሁን ወቅት የአገር ባህል አልባሳቱን የመግዛት አቅም የሌላቸው በመሆኑ ከቻይና አገር በገፍ ወደሚገባው የሽፎን አልባሳት እየሄደ መሆኑን ይጠቅሳሉ። በተለይም ቻይናውያን የኢትዮጵያን የአገር ባህል አስመስለው በሽፎን ጨርቅ ላይ ጥበቡን አትመው የሚያመርቱትን ልብስ በብዛት ይጠቀማሉ። ይህ ልብስም በአሁን ወቅት በብዛት እየተለመደ የመጣ በመሆኑ የአገር ባህል አልባሳቱን እየተካ እንዳይሄድ ያላቸውን ስጋት ጠቁመዋል። ይህም የሸመና ባለሙያውን እንዲሁም ነጋዴውን ስራ እንዳያጣ ያሰጋል ሲሉም ይጠቅሳሉ።

የአገር ባህል ልብስ ዋጋው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ መሆኑን በማስታወስ በተለይም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በከፍተኛ መጠን የጨመረ መሆኑን ወይዘሮ አልማዝ አንስተው እርሳቸው አንድ የአገር ባህል ቀሚስ ዘጠኝ ሺ ብር እንደገዙ ተናግረዋል። ከሴት ልጃቸው ጋር 18 ሺ ብር አውጥተው ሁለት የአገር ባህል ቀሚስ የገዙት ወይዘሮዋ፤ ከሌሎች የገበያ ቦታዎች (ከቦሌና አራት ኪሎ የባህል አልባሳት መሸጫ ሱቆች) ደግሞ ሽሮ ሜዳ የተሻለ እንደሆነም ጠቁመዋል። በሌሎች አካባቢዎች ብዙም ውበት ለሌላቸው አልባሳት እንኳን እስከ 10 ሺ ብር ይጠየቃል። በሽሮ ሜዳ ገበያ የሚታየው ዋጋ ከሌሎች አካባቢዎች በመጠኑ የተሻለ ከመሆኑም ባለፈ ጥራት ያላቸውና ውብ የሆኑ የጥበብ ሥራዎች ይታያሉ።

ትንሹና በቡና ማፍላት ፕሮግራም ላይ የሚለበሰው ቀለል ያለው የአገር ባህል አልባሳት በሽሮ ሜዳ ገበያ እስከ ሶስት ሺ ብር የሚሸጥ እንደሆነና እንደየደረጃቸው ስምንት ሺ አስር ሺና ከዛም በላይ በሆነ ዋጋ የሚሸጥ እንደሆነም አጫውተውናል። እኛም ተዘዋውረን እንደተመለከትነው እጅጉን ያማረና ባለሙያዎች የተጠበቡበት አይን የሚይዙ የአገር ባህል አልባሳት መኖራቸውን እና ከፍተኛ ዋጋ የሚጠራባቸው መሆናቸውን ታዝበናል።

ሌላኛዋ ሸማች ወጣት ሜላት ተሾመ ዘንድሮ የአገር ባህል አልባሳት መወደዱን ገልጻልኛለች። የዋጋው መወደድ ሰዎች ባህላዊ አልባሳቱን መጠቀም እንዳይችሉ እያደረጋቸው ነው ትላለች። በአሁን ወቅት ለበዓላት፣ ለሰርግ፣ ለግብዣና ለሌሎችም ዝግጅቶች የአገር ባህል አልባሳትን መልበስ በስፋት ይወደዳል። ነገር ግን ዋጋው በዚህ ከቀጠለ አልባሳቱን የሚጠቀም አይኖርም በማለት ሀሳቧን ገልጻለች።

የአገር ባህል አልባሳቱ በየጊዜው ዋጋው እየጨመረ ለመምጣቱ ነጋዴው የግብዓት መወደድን በምክንያትነት ቢያነሳም አሁን እየታየ ባለው ዋጋ መጠን ልክ የግብዓት እጥረትና ውድነት አጋጥሟል ማለት የማይቻል ነው። ያም ቢሆን ከፍተኛ ዋጋ እየከፈለ ከሚያመርተው ሸማኔ ጋር ሲወዳደር ነጋዴው የሚያገኘው ጥቅም የሚበልጥ እንደሆነና ሸማኔው የልፋቱን ያህል እንደማያገኝ አስተያየት ሰጪዋ ትናገራለች፡፡

የግብዓት እጥረትም ሆነ የዋጋ መናር የሚገጥመው ሸማኔ ለአገር ባህል አልባሳቱ ትልቅ ዋጋ ከፍሎና ችሎታና ጥበቡን ተጠቅሞ ያመርታል። ከሸማኔው ገዝቶ በተከራየው ሱቅ የሚሸጠው ነጋዴ ግን የሸማኔውን ያህል ሳይለፋና ሳይደክም ትልቅ ዋጋ በመጠየቅ የአገር ባህል አልባሳት ዋጋን ያስወድዳል፤ ይህም ማለት አንድ ሸማኔ ለጥበብ ሥራው ካወጣው ወጪ፣ ጉልበትና የወሰደበት ጊዜ ተደምሮ ያለው ወጪና ነጋዴው ምንም እሴት ሳይጨምር ከሸማኔው ተቀብሎ በሚሸጠው ልብስ ላይ የሚያገኘው ትርፍ ከፍተኛ እንደሆነ አስረድተዋል።

ለአገር ባህል አልባሳቱም ሆነ ለሌሎች ምርቶች ዋጋ መናር ነጋዴው አንደኛ ምክንያት እንደሆነ በማንሳትም ነጋዴው ላይ አስፈላጊውን ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ ጠቁመዋል። በተለይም በውጭ ምንዛሪ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ግብዓቶችን በማይጠይቁ ምርቶች ላይ የሚታየውን የዋጋ ንረት ለማስታረቅ የሚመለከተው አካል ቢመለከተው መልካም ነው በማለት ሀሳባቸውን ቋጭተዋል።

የአገር ባህል አልባሳት በአይነት በአይነቱ ተሰድሮ የሸማቹን አይንና ቀልብ ከሚስበው ሱቆች መካካል በአንደኛው ሱቅ ያገኘናት የአገር ባህል አልባሳት ነጋዴ ወይዘሮ ማህሌት በቀለ ትባላለች። በዘርፉ ከተሰማራች ቆየት ያለች መሆኑን ገልጻ እርሷም እንደሌሎች ከጊዜ ወደ ጊዜ የአገር ባህል አልባሳት ከነጠላ ጀምሮ በከፍተኛ መጠን እየተወደደ የመጣ መሆኑን ትገልጻለች፡፡

አጠቃላይ የገበያው እንቅስቃሴ እንዴት ነው ፍላጎቱና የዋጋው ነገርስ የሸማቹን አቅም ያገናዘበ ነው ወይ ስንል ላነሳንላት ጥያቄ ስትመልስ፤ ገበያው ከወትሮው በተለየ ሁኔታ የተሟሟቀ እንደሆነና በየጊዜው የአገር ባህል አልባሳት በእጅጉ እየተፈለገ መምጣቱን አንስታለች። ይሁንና አሁን ያለንበት ወቅትና የአገር ባህል አልባሳቱ ዋጋ ሊገናኝ አልቻለም። አሁን ላይ አልባሳቱ በጣም እየተወደደ የመጣ በመሆኑ ሰዎች አልባሳቱን ከመግዛት ይልቅ ወደ መከራየት እያዘነበሉ እንደሆነ ትናገራለች፡፡

በርካታ ተጠቃሚ ያለው የአገር ባህል አልባሳት በተለይም በአሁን ወቅት ፍላጎቱ በከፍተኛ መጠን እየጨመረ ሲሆን ዋጋውም በዛው ልክ እየጨመረ በመሆኑ ሰዎች ለሚፈልጉት ጊዜ ብቻ በኪራይ እንዲለብሱ ተገደዋል። ለዋጋው መወደድ ዋናው ምክንያትም የግብዓት መወደድ መሆኑን ያነሳችው ማህሌት፤ በአሁን ወቅት ከመደበኛ ክር አንስቶ ማንኛውም የሽመና ግብዓት ጨምሯል። ግብዓቶቹ በመወደዳቸው ምክንያትም የአገር ባህል አልባሳቱ መወደዱን ለተጠቃሚ ለማስረዳት አስቸጋሪ እንደሆነባትም ትናገራለች፡፡

እጅግ የሚያማምሩና የተዋቡ የሸማኔው የጥበብ ሥራዎች የሆኑ አልባሳት በየጊዜው የሚሰሩ እንደሆነ ያነሳችው ወይዘሮ ማህሌት፤ ዋጋው ግን የሸማቹን የመግዛት አቅም የሚፈታተንና በእጅጉ የሚያስደነግጥ እንደሆነ አልሸሸገችም። ታድያ ሰዎች የመግዛት አቅማቸውን ያማከለ እንዲሆን በግብዓቱ ላይ የሚታየው የዋጋ ንረቱ መረጋጋት አለበት። ነጋዴውም ቢሆን ምክንያታዊ የሆነ ዋጋው ሲኖር ነው በብዛት ሸጦ ማትረፍና ተጠቃሚ መሆን የሚችለው ካልሆነ ግን ሸማቹ መግዛት አይችልም፤ ሸማቹ መግዛት ካልቻለ ደግሞ ነጋዴው ከሸማኔ ገዝቶ መሸጥ ካልቻለ ትርፉ ኪሳራ እንደሚሆን ታስረዳለች፡፡

በበዓላት ወቅት እና በሰርግ ጊዜ በብዛት የሚፈለገው የአገር ባህል አልባሳት በአሁን ወቅትም በስፋት የሚፈለግ ቢሆንም ካለፉት ሁለትና ሶስት ወራት ወዲህ እንኳን የአልባሳቱ ዋጋ በእጥፍ ጨምሯል። ያለፉት ሁለት በዓላት ገናና ጥምቀት በከፍተኛ መጠን የአገር ባህል አልባሳት የተሸጠበት ዋጋውም ጥሩ የሚባል እንደነበር በማስታወስ በአሁን ወቅት ግን ዋጋው በከፍተኛ መጠን መጨመሩን ትናገራለች። ለዚህም ምክንያቱ በዋናነት መነን የተባለው ምርት መወደዱ አንዱ ሲሆን ሌላው ደግሞ የጥለት መወደድ መሆኑን ትገልጻለች።፡

ለአገር ባህል አልባሳት በዋናነት አስፈላጊ የሆነው ጥሬ ዕቃ መነን እንደመሆኑ በአሁን ወቅት ደግሞ ሸማኔው የመነን እጥረት አጋጥሞታል ። በዚህ ምክንያት የባህል አልባሳት ተወዷል። 20 እና 30 ሺ ብር የሚሸጥ የአገር ባህል አልባሳት እንዳለ ሁሉ ትንሹ ዋጋ የሚባለው ስምንት እና አስር ሺ ብር እንደሆነ በመግለጽ፤ በተለይም ፋሽን ተብሎ የሚመጡ የተለዩ ጥለቶች እስከ 50 ሺ ብር ድረስ እንደሚሸጡም ታስረዳለች፡፡

ሸማኔው የተጠበበትን የአገር ባህል በመግዛት ለገበያ የምታቀርበው ወይዘሮ ማህሌት ደንበኞቿም ይዘውት የሚመጡት ዲዛይን ካለም በሸማኔው አሰርታ እንደምትሸጥ ትገልፃለች። በብዛት ግን ሸማኔው በራሱ ዲዛይን ሰርቶ የሚያቀርብ እንደሆነና በወቅቱ የገበያ ዋጋ ገዝተው አትርፈው የሚሸጡ መሆኑንም ታስረዳለች። ሸማኔው ከሚያመጣው በተጨማሪም አብዛኛው ደንበኛ በፎቶግራፍ የተለያዩ ዲዛይኖችን ይዘው ይመጣሉ። ይሄንኑ ሸማኔውም ሰርቶ እስኪያመጣ ሰፊ ጊዜ የሚወስድበት በመሆኑ በቀጠሮ ርዝማኔ በብዛት ደንበኞች የሚሸሹበት አጋጣሚ መኖሩንም አንስታሳለች፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ሸማኔው በራሱ ዲዛይን ከሚሰራው ጥለት በላይ በፎቶግራፍ በትዕዛዝ እንዲሰራ በሚሰጠው ሥራ ላይ የሚሰጠው ዋጋ በእጅጉ ከፍ ያለ በመሆኑ ለዋጋው መወደድ አንድ ምክንያት ነው። ከዋጋው መወደድ ባለፈም ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ በትዕዛዝ የሚሰሩ አልባሳት ላይ ዋጋው ይበልጥ ይወደዳል። ለአብነትም መደበኛ የሆነ ነጠላ የዛሬ ዓመት ከ300 እስከ 400 ሲሸጥ የነበረ ሲሆን በአሁን ወቅት እስከ ሰባት እና ስምንት መቶ ብር ድረስ እየተሸጠ መሆኑን አስረድታለች።

ዘንድሮ 50 ሺ ብር ድረስ የሚሸጡ የአገር ባህል አልባሳት ማለትም ቀሚስ የዛሬ ዓመት 30 እና 35 ሺ ብር ድረስ ሲሸጡ የነበሩ ናቸው።፤ 10 እና 15 ሺ ሲሸጡ የነበሩት ደግሞ 20 እና 30 ሺ ብር እየተሸጠ ነው። በተለይም ባለፈው በጥምቀትና በገና በዓላት የነበረው ገበያ ጥሩ የነበረ መሆኑን በማንሳት በአሁን ወቅት ከፋሲካ ጾም ጀምሮ ያለው ዋጋ ግን በፍጹም የማይሞከር ነው ትላለች። ለዚህም ዋናው ምክንያት ከ37 እስከ 40 ብር ሲሸጥ የነበረው የአንድ ሜትር መነን በሁለትና ሶስት ወራት ውስጥ ብቻ ዋጋው በእጥፍ ጨምሮ በአሁን ወቅት እስከ 80 ብር እየተሸጠ ይገኛል። ይህ ለአገር ባህል አልባሳቱ መወደድ ዋናው ምክንያት እንደሆነ በማንሳት ሀሳቧን ቋጭታለች።





# የሴራው ማርከሻ

**ዋስልኝ አየለ**

ሰሞኑን በአገራችን የተለያዩ አካባቢዎች ግርግሮች ተፈጥረው ታይተዋል፤ በጎንደር በአንድ የእስልምና እምነት አባት ቀብር ስነስርአት ወቅት በአንዳንድ የክርስትና እና የእስልምና እምነት ተከታዮች መካከል የተከሰተን አለመግባባት ምክንያት በማድረግ በተቀሰቀሰ ግርግር በሙስሊሞች ላይ አስነዋሪ ድርጊት ተፈጽሟል። ድርጊቱን ፈጽመዋል በሚል የተጠረጠሩ ከሁለት መቶ በላይ ሰዎችንም የክልሉ መንግሥት በቁጥጥር ሥር አውሏል። ግርግሩ አንዳንድ ከተሞችን እየነካካና እያስፈራራ አዲስ አበባም ጎራ ብሏል።

የጎንደሩ ድርጊት በቁጥጥር ሥር ውሎ፤ ተጠርጣሪዎችም ተይዘዋል በተባለበት ሁኔታ፤ ጥፋትን በጥፋት ለመመለስ በተደረገ ሙከራ ተጨማሪ ጥፋቶች በስልጤ ዞን ወራቤ ተፈጽሟል። በዚህም የሰው ሕይወት ጠፍቷል፤ አብያተ ክስርቲያናት ተቃጥለዋል። እነዚህ ተጨማሪ ጥፋቶች ደግሞ የሽብር ድርጊት የተጫናቸው ሃይማኖትን ሽፋን ያደረጉ ፖለቲካዊ ዓላማዎች ያላቸው ናቸው።

ግርግሩን በየአካባቢው ለማስነሳት እንደመሞከሩ የተቀናጀ ነበር ለማለት ያስደፍራል፤ በአዲስ አበባ በኢድአልፈጥር በአል ላይ በመስቀል አደባባይ የተከሰተው ግርግር በንብረትና በጸጥታ ኃይሎች ላይ ጉዳት አስከትሏል። በከተማዋ ከበአሉ ከሁለት ቀናት ቀደም ብሎ ከአፍጥር ስነስርአት በሁዋላም በአንዳንድ አካባቢዎች የማወክ ድርጊቶች ታይተዋል።

ከትናንት በስቲያ ከሽሮ ሜዳ ወደ እንጦጦ ኪዳነ ምህረት እየሄድኩ ነበር። ታክሲ ውስጥ አንድ የእስልምና እምነት ተከታይ ሕጻን ልጅ ይዘው ገቡ። በማህበራዊ ገጾች ሲዘዋወር የነበረውን ተንቀሳቃሽ ምስል እና ፎቶዎች ብዙ ሰው አይቶ ስለነበር ምን እንደተፈጠረ ስለሁኔታው ጠየቅናቸው። በእውነቱ ምን ተፈጥሮ እንደሆነ አያውቁም፤ እርሳቸው የሚያውቁት ግርግርና ወከባ መፈጠሩን ብቻ ነው።

እርግጥ ነው እርሳቸው ብቻ ሳይሆኑ አብዛኛው ወደቦታው የሄደው ሰው ይህን አያውቅም፤ ይህን የሚያውቁት ተልዕኮ ይዘው የሄዱ ጥቂት አካላት ብቻ ናቸው። ለዚህ ደግሞ ምስክሩ አብዛኛው የእስልምና እምነት ተከታዮች ሕጻናት ልጆቻቸውን ይዘው መሄዳቸው ነው። መቼም ሁከትና ግርግር ያሰበ ሰው ሕጻን ልጁን ይዞ ይሄዳል ተብሎ አይታሰብም። በተፈጠረው ግርግር በርካታ ሕጻናት ከወላጆቻቸው ተነጥለው የማፈላለግና የማገናኘት ሥራዎች ሲሰሩ ውለዋል።

የጠፋው የሰው ህይወትና የወደሙ ንብረቶች ሲታሰቡ ግርግሮች ጉዳት እንጂ የሚያመጡት ጥቅም እንደሌለ እንረዳለን፤ እርግጥ ነው ግርግር የሚጠቅመው ለሌባ ነው፤ ግርግር የሚጠቅመው ራሱን ግርግር ፈጣሪውን ብቻ ነው። ህብረተሰቡን አይጠቅምም፤ ህብረተሰቡ ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው ነገሮች በሰላማዊ መንገድ ብቻ ሲፈጸሙ ነው።

የጠላቶቻችን እጆች አሳምረን እናውቃለን፤ እነ ጭር ሲል አልወድም አሁንም አለመተኛታቸውን ከእነዚህ ግርግሮች መረዳት አያዳግትም። ግርግሮቹ የውጭና የአገር ውስጥ ጠላቶቻችን ተላላኪዎችና ጥቅመኞች ሴራ ነው። በተላላኪዎቻቸው ባለፉት አመታት በርካታ የሽብር ድርጊቶች ፈጽመዋል። ግርግሮቹም የዚያው ሴራ ሌላ ምእራፍ ነው።

እንዲያ ካልሆነ ታዲያ የራስን ንብረት ማውደም፣ የሌላን እምነት ተቋም ማቃጠል ለማን ይጠቅማል? የሌላን እምነት ተቋም ማቃጠል በአጸፋው የራስ ወገን የእምነት ተቋም ጉዳት እንዲደርስበት በር መክፈት መሆኑስ እንዴት ይዘነጋል? ለነገሩ አሸባሪና ተላላኪው ለእዚህ ግድ የላቸውም፤ የሰው ህይወት ጠፋ፣ አካል ጎደለ፣ ንብረት ተዘረፈ፣ ተቃጠለ የሚሉት ለእነሱ ጉዳያቸው አይደሉም፤ ሕጻናትና ሴቶች አዛውንቶች በተገኙበት ታላቅ በአል ላይ ግርግር በመፍጠር የጥፋት አላማን ለማሳካት ሲንቀሳቀሱ አላማችንን ለማሳካት ሁነኛው ቀዳዳ ይሄ ነው ብለው ነው።

ከትናንት በስቲያ መስቀል አደባባይ ከተፈጠረው ግርግር ብዙ ነገሮችን ታዝቤያለሁ። የበአሉ ታዳሚዎች የግርግሩን መነሻ በተመለከተ የተለያዩ አስተያየቶችን ሰጥተዋል፤ በመንግሥት በኩል በተሰጠው መግለጫ ችግሩ ሁከትና ግርግር መፍጠር በፈለጉ ሰዎች የተፈጠረ ነው ተብሏል። በዕለቱ ብቻ በዚህ ድርጊት የተሳተፉ 76 ሰዎች በቁጥጥር ሥር መዋላቸውም በመንግስት ተገልጸል።

በግርግሩ የቀይ ሽብር ሰማዕታት ሀውልትን ጨምሮ በባንኮችና ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ ጉዳት ደርሷል። ይህ የሚያመለክተው ድርጊቱ ታስቦበት መፈጸሙን ነው። በአካባቢው የታዩ መፈክሮችና ምስሎች ተጨማሪ ማሳያዎች ናቸው። ‹‹የአጼውን ሥርዓት ቀብረነዋል›› የሚል ጽሑፍ ያለበት ከካርቶን የተዘጋጀ የሬሳ ሳጥን ቅርጽ ተይዟል። ከሥር ስድብ የተጻፈባቸው የመገናኛ ብዙኃን አርማ እና ሌሎች መፈክሮች ነበሩ። እነዚህ ነገሮች ታስቦባቸው የተዘጋጁ እንጂ በቅጽበት የተፈጠሩ አይደሉም።

እንግዲህ ሕዝበ ሙስሊሙ በሰላማዊ መንገድ በዓሉን ሊያከብር ሲሄድ የራሳቸውን ፖለቲካዊ ዓላማ ለማሳካት ተቀላቅለው የሄዱ ነበሩ ማለት ነው፤ አማኙ ይህን ያደርጋል ተብሎ አይታሰብም። ሃይማኖታዊ በዓል በሚከበርበት ዝግጅት ላይ እንደዚያ አይነት መፈክሮች ተይዞ ሊወጣ አይችልማ።

ሌላው የታዘብኩት በርካታ የእምነቱ ተከታዮች ግርግሩን ለማስቆምና መረጋጋት ለማምጣት እጆቻቸውን ዘርግተው ‹‹አባካችሁ!›› እያሉ መማጸናቸውን ነው። በእርግጥም እነዚህ የሰላም መልእክተኞች በማህበራዊ ሚዲያዎች የበአሉ ታዳሚ ሙስሊም እንዲረጋጋ ሲጥሩ ታይተዋል፤ አረ እነዚህ ሰዎች ይብዙልን፤ ግርግሩ በቀላሉ በቁጥጥር ሥር የዋለውም በእነዚህ አማኞች ሰላም ፈላጊነት ጭምር ነው ማለትም ይቻላል፤ ለእዚህ ተግባራቸው በእጅጉ ሊመሰገኑ ይገባቸዋል።

ግርግሩን አስበውበትና ተዘጋጅተውበት የሄዱ ስለመኖራቸው ግን ጥርጥር የለውም፤ ያ ባይሆን ኖሮ ሃይማኖታዊ በዓል ላይ ግጭት ቀስቃሽ ምልክቶች ባልተገኙ ነበር። የፀጥታና ደህንነት የጋራ ግብረ ኃይሉ ‹‹እነዚህ ፀረ ሰላም ግለሰቦችና ቡድኖች ሀይማኖትን ሽፋን በማድረግ ተደራጅተው በአንዳንድ አካባቢዎች ስለታማ ነገሮችን፣ የውጭ አገር አክራሪዎችን አርማና የተለያዩ ግጭት ቀስቃሽ ጽሁፎችን በመያዝ ጥቃትና በቀል ለመፈፀም ወደ በዓሉ ስፍራ መምጣታቸውን ግብረ ኃይሉ በቁጥጥር ስር ካዋላቸው ፀረ ሰላም ኃይሎች እጅ ይዟል›› ሲል ከገለጸው መረዳት የሚቻለውም ይህንኑ ነው፡፡

በተንቀሳቃሽ ምስሎች ከታዩት ግጭት ቀስቃሽ ጽሁፎችና ምስሎች በተጨማሪ ስለታማ ነገሮች ሁሉ መኖራቸው ምን ማለት እንደሆነ ማንም ይገነዘበዋል። ሰላም ወዳዱ አማኝ እና የፀጥታ ኃይሉ በቀላሉ ባይቆጣጠሩት ኖሮ የታሰበው ከፍተኛ ብጥብጥ መፍጠር ነበር ማለት ይቻላል፡፡

ድርጊቱ ሴራና ሽብር የተጫነው ለመሆኑ ደግሞ ሌላኛው ምልክት በዕለቱ ማታ የተሰማው ዜና ነው። ዜናው፤ የጦር መሳሪያ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሞከሩ የአልሸባብ ቡድን አባላት በቁጥጥር ስር መዋላቸውን ያመለክታል። በሶማሌ ክልል አፍዴር ዞን ኤልከሬ ወረዳ ለሽብር ጥቃት ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሞከሩ የአልሸባብ ቡድን አባላት ከጦር መሳሪያ እና ጥይቶቻቸው ጋር በቁጥጥር ስር መዋላቸውን የሶማሌ ክልል ልዩ ኃይል በዕለቱ አስታውቋል። ይህም ሌላው የሽብር ሴራ ማሳያ ነው። አሁን ነገሩ የሽብር እንቅስቃሴ መሆኑ ግልጽ ሆኗል። ይህ ለመሆኑ ከዚህ በላይ ግልጽ ማሳያዎች አይኖሩም፡፡

የጠላቶቻችን ሴራ ከሽፏል፤ በቀጣይም ከሁላችንም የሚጠበቀው ሰላም ፈላጊ መሆን ብቻ ነው። ለዚህ ደግሞ ሁሉም ሃላፊነት አለበት። በፀጥታ አካላት ላይ ብቻ የተጣለ ሥራ አይደለም። የእኔ ሃይማኖት የሚከበረው የሌላው ሃይማኖት ሲከበር ነው። ጥፋትን በጥፋት ለማካካስ መሞከርም ሌላ ተጨማሪ ጥፋት ማስከተል ነው። ስለዚህ ሁሉም ይህን ልብ ሊል ይገባል፡፡

መንግሥትም የፀጥታ ሃይሉን ማጠናከር አለበት፤ በተለይም ከሽብር ድርጊት ጋር የሚያያዙ የትኛውንም ሃይማኖት ይሁን ብሄርን ሽፋን አድርገው የሚንቀሳቀሱ ሃይሎችን መታገስ የለበትም። ከትናንት በስቲያ በተፈጠረው ችግር ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች መግለጫ አውጥተዋል፤ የመግለጫቸው ይዘትም ድርጊቱ የአሸባሪ ኃይሎችን ተልዕኮ የሚያራምዱ ሰዎች እንቅስቃሴ መሆኑን ጠቁሟል። ስራቸው መግለጫ ከማውጣት በተጨማሪ ከህዝቡ፣ ከጸጥታ ኃይሎችና ከፌዴራል መንግሥቱ ጋር በቅንጅት መስራትም ይኖርባቸዋል። በአዲስ አበባ የኢድ አልፈጥር በአል ሲከበር የተፈጠረውን ግርግር ለማስቆምና ህዝቡን ለማረጋጋት ሙስሊሙ ህብረተሰብ ያደረገው ጥረት ትምህርት ሊወሰድበትና ሊሰፋ የሚገባው ነው። ይህ ርብርብ የአሸባሪንና ተላላኪውን ሴራ በቅንጅት ማርከስ እንደሚቻል አሳይቷል፤ በቀጣይም በእዚህ መልኩ ነው መስራት ያለበት፡፡

# ዓለም አቀፍ

## ላቭሮቭ “ሂትለር አይሁዳዊ ነው” ማለታቸውን ተከትሎ እስራኤል ሩሲያ ይቅርታ እንድትል ጠይቃለች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



እስራኤል፤ የሩሲያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሰርጌ ላቭሮቭን የናዚ መሪ አዶልፍ ሂትለር “አይሁዳዊ ነው” ሲሉ የሰጡት አስተያየት ጸረ ሴማዊነት እና አደገኛ ነው ስትል ወቀሰች።

የእስራኤል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ያየር ላፒድ በእስራኤል የሚገኙትን የሩስያ አምባሳደር፤ ላቭሮቭ እሁድ እለት ከጣሊያን ቴሌቪዥን ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ስላሉት የተሳሳተ ንግግር ማብራሪያ ለመስጠት እንደሚጠሩ አስታውቀዋል።

ላፒድ ዋይ ኔት ለተባለ የዜና ድረ-ገጽ እንደተናገሩት “ይህ ይቅር የማይባል፣ አሳፋሪ መግለጫ፣ አሰቃቂ ታሪካዊ ስህተት ነው፣ እናም ከሩሲያ ይቅርታ እንጠብቃለን” ብለዋል።

እስራኤል በላቭሮቭ ንግግር እጅጉን እንደተበሳጨች በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴሯ በኩል ብትገልጽም፤ ከሩሲያ ኤምባሲ እስካሁን የተሰጠ ምንም አይነት አስተያየት የለም።

ሬቴ 4 ቻናል ከተባለ የጣሊያን ቴሌቪዥን ጋር በአንድ ጣሊያናዊ አስተርጓሚ አማካኝነት ቆይታ ያደረጉት ላቭሮቭ፤ ስለ ሂትለር የተናገሩት ጋዜጠኛው፤ ሩሲያ አሁን በዩክሬን የምታደርገውን ወታደራዊ ዘመቻ “ዩክሬንን ከናዚ ለማዳን” የምትለው ለምንድን ነው? ተብለው ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ ነው።

ጋዜጠኛው አስከትሎ ላቭሮቭን “የአገሪቱ ፕሬዚዳንት ቮሎዲሚር ዘለንስኪ አይሁዳዊ እንደሆኑ እየታወቀ እንዴት ከናዚዝም እናድናታለን ትላላችሁ?” የሚል ጥያቄ አቅርቦላቸዋል።

የላቭሮቭ ምላሽ ግን “ሂትለርም እኮ አመጣጡ ከአይሁድ ነው፣ ስለዚህ ምንም ማለት አይደለም” የሚል ነበር።

ይህ ብቻ አይደለም ላቭሮቭ “ጥበበኞቹ የአይሁድ ሰዎችም፤ ትልቁ ጸረ-ሴማዊነት የሆኑት እራሳቸው አይሁዶች ናቸው ይላሉ “ የሚል መከራከሪያም አቅርቧል።

የላቭሮቭ ንግግር እስራኤልን አስቆጥቷል።

እስራኤል ለዩክሬን ደጋግማ እንደምትደግፍ ገልጻላች፣ ነገር ግን በጎረቤት ሶሪያ ከባድ ተጽእኖ የመፍጠር አቅም ካላት ሩሲያ ጋር ያለው ግንኙነት እንዳይበላሽ ጥንቃቄ ስታደርግ ቆይታለች።

ለዚህም ነው ምእራባውያኑ በሩሲያ ላይ ማእቀብ ሲያዘንቡ፤ እስራኤል ድርጊቱን ከማውገዝ በዘለለ ምንም ስትል ስታስፈጽም ያልታየችው።



## ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ኬንያታ ምክትላቸው ዊሊያም ሩቶን “ስልጣን ልቀቅ” አሉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የኬንያው ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ኬንያታ የአገሪቱ ምክትል ፕሬዚዳንት ዊሊያም ሩቶ ሥልጣናቸውን በፍቃዳቸው እንዲለቁ መጠየቃቸው ተሰምቷል።

ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ኬንያታ ምክትላቸው የሆኑት ዊሊያም ሩቶ “ኬንያ ካጋጠማት የኢኮኖሚ ቀውስ እንድትወጣ የሚጠበቅባቸውን አልሰሩም” በሚል ይከሷቸዋል።

የኬንያ ምክትል ፕሬዚዳንት ዊሊያም ሩቶ መንግስትን ከውስጥ ሆነው መተቸት እንደሌለባቸውም ኡሁሩ ኬንያታ ተናግረዋል።

ምክትል ፕሬዚዳንት ሩቶ በበኩላቸው ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ የኬንያ መንግስት ካቢኔ ተሰብስቦ እንደማያውቅ እና የመንግስት ውሳኔዎች በፕሬዚዳንቱ የስልክ ጥሪ ብቻ እንደሚተላለፉ በትዊተር ገጻቸው አስታውቀዋል።

ኬንያ የፊታችን ነሃሴ ወር ላይ ከምታደርገው በፕሬዚዳንታዊ ምርጫ በፊት በሁለቱ መካከል ያለው የከረረ አለመግባባት ይፋ መውጣቱ ተነግሯል።

በፕሬዚዳንቱ እና በምክትል ፕሬዚዳንቱ መካከል ያለው ልዩነት ገሃድ የወጣውም የአገሪቱ የቀድሞ ፕሬዚዳንት ሞዋይ ኪባኪ ሞትን ተከትሎ በነበረው የሀዘን ስነ ስርዓት ላይ ነበር።

ባሳለፍነው ሳምንት አርብ በነበረው የቀድሞ ፕሬዚዳንት ስርዓተ ቀብር ላይም ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ኬንያታ የምክትላቸውን ዊሊያም ሩቶን እጅ ለመጨበጥ ፍቃደኛ ሳይሆኑ ሲቀሩ ተመልክቷል።

ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ኬንያታ ምክትላቸውን ከኃላፊነት የማባረር ስልጣን የላቸውም የተባለ ሲሆን፤ የአገሪቱ ምክትል ፕሬዚዳንት ከስልጣን ሊነሳ የሚችለው ከተከሰሰ ወይም አቅም ከሌለው ብቻ ነው።

የኬንያ ምክትል ፕሬዚዳንት ዊሊያም ሩቶ የፊታችን ነሃሴ ወር በሚካሄደው አጠቃላይ ምርጫ ላይ ለፕሬዚዳንትነት ለመወዳደር በእጩነት መቅረባቸው ይታወሳል።

የስልጣን ዘመናቸው ማጠናቀቂያ ላይ የሚገኙት ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ኬንያታ ከምክትላቸው ይልቅ ለቀድሞ ተቀናቃኛቸው ራይላ ኦዲንጋ ድጋፍ መስጠታቸው ይታወሳል።

ይህንን ተከትሎም ምክትል ፕሬዚዳንት ዊሊያም ሩቶ፤ ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ኬንያታ “ማንንም መደገፍ መብታቸው ነው፤ ምርጫውን ግን እኛ እናሸንፋለን” ሲሉ ተደምጠው ነበር።

የኡሁሩ ኬንያታ እና የዊሊያም ሩቶ አለመግባባት መነሻም የፊታችን ነሃሴ ወር የሚካሄደው ምርጫ ጉዳይ ሳይሆን እንዳልቀረ መላ ምቶች ተቀምጠዋል።

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## ኪዳኔ ወልደመድኅን - የማይበገረው አርበኛ

**አንተነህ ቸሬ**



ኢትዮጵያ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ በተለያዩ ጊዜያት በርካታ ጀግኖችን ያፈራች አገር ናት። ወራሪ ኃይሎች የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት በመዳፈር በመዳፋቸው ስር ሊያስገቧት አስበው ብዙ ሞክረዋል። መሰል ተደጋጋሚ ሙከራዎችን ካደረጉት ወራሪዎች መካከል አውሮፓዊቷ ኢጣሊያ በግንባር ቀደምትነት ትጠቀሳለች። የፍራንቼስኮ ክሪስፒዋ ኢጣሊያ ዓድዋ ላይ የተከናነበችውን የሽንፈት ካባ በድል ለማካካስ በማሰብ በፋሺስቱ ቤኒቶ ሙሶሎኒ እየተመራች አሰቃቂ ወረራ በመፈፀም ለአምስት ዓመታት ያህል ኢትዮጵያን ቅኝ ተገዢዋ ለማድረግ ጥረት አድርጋም ነበር፡፡

ኢጣሊያ ዓድዋ ላይ የተከናነበችውን ሽንፈት ለመበቀል ለአርባ ዓመታት ያህል ስትዘጋጅ ከኖረች በኋላ በየጊዜው ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በባህል መስክ የተፈራረመቻቸውን የሰላምና የትብብር ውሎችና በመንግሥታቱ ማኅበር አባልነቷ የገባቻቸውን ዓለም አቀፍ ግዴታዎች ሁሉ በጠመንጃ አፈሙዝ መቅደድ ጀመረች፡፡

እንዲህ እንዲህ እያለች በ1928 ዓ.ም ኢትዮጵያን ወረረች። ታዲያ መቼውንም ቢሆን በአገሩና በነፃነቱ የማይደራደረው የኢትዮጵያ ሕዝብ የፋሺስትን አገዛዝ «አሜን» ብሎ አልተቀበለውም። ይልቁንም ጨርቄን ማቄን ሳይል «ጥራኝ ዱሩ» ብሎ ለነፃነቱ መፋለም ጀመረ። የኢጣሊያ ወራሪ ኃይልም አንዲትም ቀን እንኳን እፎይ ብሎ ሳይቀመጥ ከአምስት ዓመታት እልህ አስጨራሽ ትግል በኋላ ሌላ የሽንፈት ማቅ ለብሶ ከኢትዮጵያ ምድር ተባረረ። ታዲያ በዚህ አስገራሚና አኩሪ የመስዋዕትነት ጉዞ ውስጥ ደማቅ የጀግንነት ታሪክ ከፃፉና ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ከተጋደሉ እልፍ የኢትዮጵያ ጀግኖች መካከል አንዱ ታላቁ አርበኛ ደጃዝማች ኪዳኔ ወልደመድኅን ነበሩ።

ኪዳኔ ወልደመድኅን በዕለተ ዓርብ፣ ሐምሌ 2 ቀን 1907 ዓ.ም ቡልጋ ከሰም ወረዳ፤ የለጥ ቀበሌ፤ ልዩ ስሙ ቡሄ አምባ በሚባለው ሥፍራ ላይ ከእናቱ ከወይዘሮ አስካለ ደጀን እና ከአባቱ ከቀኛዝማች ወልደመድኅን አዩደረስ ተወለደ። አባቱ ቀኛዝማች ወልደመድኅን በዘመኑ የታወቁ ስመጥር ጠበቃ ነበሩ። ኪዳኔ ማርያም እስከ 12 ዓመት እድሜው ድረስ እዚያው ቡሄ አምባ አካባቢ በአያቱ አቶ ደጀን ደብሩ ቤት ሆኖ የቄስ ትምህርት በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተከታትሏል። በመቀጠልም ከወላጆቹ ጋር ሆኖ የአማርኛና የግእዝ ትምህርቱን አጠናቋል።

ለአካለ መጠን ሲደርስ በ18 ዓመቱ በ1925 ዓ.ም. አዲስ አበባ የክብር ዘበኛ ሰራዊት አባል ሆነ። ወዲያው በንጉሠ ነገሥቱ ትዕዛዝ ከ69 አዲስ ወታደሮች ጋር ባሌ ተመድቦ እስከ 1927 ዓ.ም ድረስ በተራ ወታደርነት ከዚያም በሃምሳ ዓለቃነትና በባሻነት ማዕረግ ሲያገለግል ከቆየ በኋላ የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ኢትዮጵያን በወረረበት ጊዜ በ1928 ዓ.ም በነደጃዝማች በየነ መርድ መሪነት ከጎባ ወደ ኦጋዴን ዘመተ።

ኪዳኔ ከባላምባራስ አየለ ወልደማርያምና ሌሎች አርበኞች ጋር ሆኖ በዚህ ግንባር በዋቢ ሸበሌና አካባቢው ለዘጠኝ ወራት ያህል ከጠላት ጋር ሲፋለም ከርሞ ወደ ጎባ ተመለሰ። ከሰኔ 1928 ዓ.ም እስከ ሚያዝያ 1929 ዓ.ም ድረስ ከአርሲ፣ ከሲዳማ፣ ከሐረርና ከኦጋዴን ወደ ጎባ የዘለቀውን የጠላት ጦር ሲዋጉ ከርመው፤ መጨረሻ ላይ ተማም ከሚባለው ሥፍራ ላይ በተካሄደው ጦርነት ላይ ማምለጥ በማይቻልበት ሁኔታ ኪዳኔና ሌሎች አርበኞች በጠላት እጅ ወድቀው ተማረኩ። ጠላትም ለአምስት ወራት በጽኑ እሥራት ከያዛቸው በኋላ፤ በጥር ወር 1930 ዓ.ም ከጎባ ወደ ወሊሶ አዛውሮ አሰራቸው።

ባሻ ኪዳኔም እዚሁ እስር ቤት እያሉ አብረዋቸው ከታሰሩት አርበኞች መካከል በምስጢር 100 ሰዎችን አደራጅተው እዚያ ያለውን የጠላት ጦር ፈጅተው ለመሸፈት ከወሰኑ በኋላ በወቅቱ ከስመ ጥር አርበኞች መካከል አንዱ ወደነበሩት ወደ ባላምባራስ (በኋላ ደጃዝማች) ገረሱ ዱኪ ሰው ለመላክ በመዘጋጀት ላይ ሳሉ አሳሪያቸው የፋሺስት ጦር ነገሩን በመስማቱ እጅግ ጥብቅ የሆነ ክትትል ይደረግባቸው ጀመር። ባሻ ኪዳኔም ይህን ሲገነዘቡ ካደራጇቸው 100 ሰዎች መካከል 55 ወታደር ከነመሳሪያው፤ አራት መትረየስ፤ አስር ሣጥን ጥይት፤ ስድስት ሽጉጥ ከጠላት እጅ ነጥቀው እየተታኮሱ ሲወጡ የጠላት ኃይል ሃያ ወታደርና አንድ መትረየስ ከሁለት ሣጥን ጥይት ጋር ብቻ ገንጥሎ ሲያስቀርባቸው ከተረፈው መሳሪያና ወታደር ጋር ድል አድርገው ሸፈቱ። ወዲያውም ኩሳ ኪዳነምሕረት ከሚባል ሥፍራ ላይ ከደጃዝማች ገረሱ ጋር ተገናኙ።

ባሻ ኪዳኔ ከባላምባራስ ገረሱ ጋር ከተቀላቀሉ በኋላም እስከ ጥቅምት 1931 ዓ.ም ድረስ በደንዲ፤ በሶዶ፤ በበዳቁሮ እና በሌሎች ሥፍራዎች በአርበኝነት ሲዋጉ ቆዩ። በዳቁሮ ከሚባለው ሥፍራ ላይ ሳሉ ሙሴ ሰባስቲያኖ ካስታኛ (ሙሴ ቀስተኛ) የሚባለው ጣሊያናዊ ከፋሺስት አመራሮች ተልኬያለሁ ብሎ ከሦሥት ባላባቶች ጋር መጣ። አርበኞቹም ይህ ሰው ቀደም ሲል በ1930 ዓ.ም ወደ ራስ አበበ አረጋይ ዘንድ ሄዶ የጦሩን ኃይል ከተመለከተ በኋላ ብዙ አርበኛ እንዳስገደለ ሰምተው ስለነበር እነሱንም እንደዚሁ ለማስፈጀት እንደመጣ ስለተገነዘቡት ባሻ ኪዳኔ ወልደመድኅን በመውዜር ጠመንጃ ሲመቱት «ኢጣልያ ለዘለዓለም ትኑር! ለኢጣሊያ ስል ሞትኩላት» ብሎ ሲናገር በሽጉጥ ራሱን መትተው ከገደሉት በኋላ የለበሰውን ሙሉ ገበርዲን ልብስና ካፖርት እንዲሁም የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ስዕል ያለበትን የብር ሰዓቱንና በቅሎውን ከነኮርቻው ማረኩት። ከሙሴ ካስታኛ ጋር አብረው የመጡት ባላባቶች የሙሴን መገደል ለፋሺስት ጦር መሪዎች አሳወቁ። ከ25 በላይ የጦር አውሮፕላኖች ያሉበት በርካታ የፋሺስት ጦር ወደ በዳቁሮ ዘመተ። አርበኞቹም ለሦስት ቀናት ሙሉ ሲከላከሉ ከቆዩ በኋላ ከሥፍራው ሸሽተው ሶዶ ላይ ለስምንት ቀናት ያህል ተዋጉ።

ባሻ ኪዳኔ በኅዳር ወር 1931 ዓ.ም. አርበኞቻቸውን አስከትለው ወደ ትውልድ አገራቸው ቡልጋ ገቡ። በዚያም ከፊታውራሪ ኃይለማርያም ማናህሌ እና ከፊታውራሪ ተረፈ ማናህሌ ጋር ተቀላቅለው እስከ መጋቢት 1931 ዓ.ም. ድረስ በውሽንግር፤ ጨፌ ዶንሳ ምሽግ፤ ነጭ ድንጋይ ምሽግ፤ ልዝብ ድንጋይ በተባሉ ቦታዎች ላይ ከጠላት ኃይል ጋር ሲዋጉ ከረሙ። በዚህ ወቀት ታመው በነበረበት ጊዜ የፋሺስት ጦር በሦስት አቅጣጫ ከበባቸው። የጠላት ኃይል እጅ እንዲሰጡ ቢጠይቃቸውም ፍቃደኛ ባለመሆናቸው ከህመማቸው ጋር እየታገሉ ከፋሺስት ጋር ተፋለሙ። በወቅቱ ባሻ ኪዳኔ ከፋሺስት ጦር ጋር ያደረጉት ፍልሚያ እጅግ መራራና እልህ አስጨራሽ እንደነበር ስለአርበኞች ታሪክ የተፃፉ መዛግብት ይመሰክራሉ። ከህመም ጋር እየታገሉ ከፋሺስት ጦር ጋር የተፋለሙት ባሻ ኪዳኔ የጠላት ጦር እርሳቸው መሸገውበት የነበረውን ጫካ በእሳት ነበልባል ግራና ቀኙን ሲያቃጥልው እሳቸው በተዓምር ተረፉ። ከሦስት ቀናት በኋላ የጠላት ኃይል አካባቢውን ለቆ ሲሄድ ባሻ ኪዳኔ ህመሙና ድካሙ በርትቶባቸው ስለወደቁ በብዙ ፍለጋ ነበር የተገኙት።

ከዚህ በኋላ ክረምቱን ቡልጋ ውስጥ በነጭ ድንጋይ፣ ፍልፍል አፈር፣ ጦስኝ ምሽግ እና በመስኖ ከነደጃዝማች ኃብተ ሥላሴ በላይነህ፣ ፊታውራሪ በለጠ ሳሴ፣ ፊታውራሪ አኅናፍርና ሌሎችም ስመጥረ የቡልጋ ልጆች ጋር ሆነው ጠላትን ሲያጠቁና ሲከላከሉ ቆይተው በመስከረም 1932 ዓ.ም በሰገሌ በኩል ተጉዘው ገሊላ ከሚባል ሥፍራ ላይ ከራስ አበበ አረጋይ ጦር ጋር ሲቀላቀሉ ባሻ ኪዳኔ የግራዝማችነት ማዕረግ ተሾሙ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ወደ ጎጃምና ወደ ጎንደር እስከዘመቱበት 1933 ዓ.ም ድረስ ከራስ አበበ ጋር ጠላትን በየቦታው ሲዋጉ በአርበኝነት ቆዩ። ከብዙ ውጊያዎችና ጀብዱዎች በኋላ በየካቲት 1933 ዓ.ም መሶቢት ከሚባለው ቦታ ላይ በመሪነት የጠላትን ጦር ድል አድርገው ወደ ዋናው ሰራዊት ከተቀላቀሉ በኋላ ራስ አበበ የቀኛዝማችነት ማዕረግ ሾሟቸው።

ቀኛዝማች ኪዳኔ ከሌሎች አርበኞች ጋር ሆነው በ1933 ዓ.ም ዳውንት፣ ተንታ እና ደብረታቦር ላይ የሰፈረውን የፋሺስት ጦር እየማረኩ በመስከረም 1934 ዓ.ም ጉማራ ላይ ከፍ ያለ ውጊያ አድርገው ጠላትን ድል አደረጉ። በኅዳር 1934 ዓ.ም ከጎንደር እስከ ቁልቋል በር ላለው ለጠላት ጦር ስንቅና ትጥቅ አቀብሎ ሲመለስ ጥቃት ከፍተውበት ብዙ ባንዳዎችን ገደሉ።

በዚያው በኅዳር ወር 1934 ዓ.ም ጎንደር ከተማ ውስጥ ጄነራል ናሲ የተባለው የፋሺስት ጦር አዛዥ ከብዙ ሺህ ሰራዊት ጋር አካባቢውን በሽቦ አጥሮ በሽቦው ውስጥና ውጭ ፈንጂና ቦንብ ቀብሮበት ነበር። ቀኛዝማች ኪዳኔ ይህንኑ የተቀበረ ቦንብ እየቆረጡ ሌሊቱን ተጉዘው ከምሽጉ ደረሱ። ሲነጋ ተኩስ ተከፈተ። ጠላትም ከከፍተኛ ተራራ ላይ ወደታች ወደነ ቀኛዝማች ኪዳኔ በቦምባርድና ከባድ መትረየስ ሲያጠቃቸው በተራራው ሥር አድርገው ወደ ጎንደር ከተማ የሚወስደውን መንገድ ላይ ሲደርሱ ከጎንደር ከተማ የሚመጡ አስመስለው ከኋላው በጨበጣ የእጅ ቦንብ እየጣሉ ብዙ የጠላት ኃይል ደመሰሱ። እንዲሁም መትረየሶችን ማርከውና ምሽጉን አስለቅቀው ከያዙ በኋላ ጀነራል ናሲ ወዳለበት ወደ ጎንደር መዳዝ ቀጠሉ። ጎንደር ሲገቡም ፋሲል ግንብ ምሽግ ሲደርሱ ምሽጉን ለመድፈር የእጅ ቦንብ ምሽጉ ላይ በብዛት ሲጥሉ ጠላት ተሸንፎ የሰላም ባንዲራ አውለበለበ። ወዲያውኑ 500 የጠላት ወታደሮችን ማረኩ። በከተማው የሚገኙትን የዓረብ ተወላጆች ሱቅና ገንዘብ እንዳይዘረፍ በወታደር አስጠብቀው ወደ ቀጣዩ ዘመቻቸው አቀኑ።

በዚያው በኅዳር ወር 1934 ዓ.ም ጎንደር ከተማ ውስጥ ጄነራል ናሲ የተባለው የፋሺስት ጦር አዛዥ ከብዙ ሺህ ሰራዊት ጋር አካባቢውን በሽቦ አጥሮ በሽቦው ውስጥና ውጭ ፈንጂና ቦንብ ቀብሮበት ነበር፡፡ ቀኛዝማች ኪዳኔ ይህንኑ የተቀበረ ቦንብ እየቆረጡ ሌሊቱን ተጉዘው ከምሽጉ ደረሱ፡፡ ሲነጋ ተኩስ ተከፈተ፡፡ ጠላትም ከከፍተኛ ተራራ ላይ ወደታች ወደነ ቀኛዝማች ኪዳኔ በቦምባርድና ከባድ መትረየስ ሲያጠቃቸው በተራራው ሥር አድርገው ወደ ጎንደር ከተማ የሚወስደውን መንገድ ላይ ሲደርሱ ከጎንደር ከተማ የሚመጡ አስመስለው ከኋላው በጨበጣ የእጅ ቦንብ እየጣሉ ብዙ የጠላት ኃይል ደመሰሱ

ኅዳር 19 ቀን 1934 ዓ.ም ራስ ብሩ ወልደብርዔል ከእንግሊዛዊው ሜጀር ጀኔራል ፎክስ ጋር ወደ ጎንደር ገቡ። «ባለህበት እርጋ» ተባለና ሁሉም ተረጋጋ። ጀኔራል ናዚ ያለድርድር እጁን ሰጠ። የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በፋሲለደስ ግንብ ላይ ተውለበለበ። በማግሥቱ ኅዳር 20 ቀን ልዑል አልጋወራሽ አስፋወሰን ኃይለሥላሴ ጎንደር ገቡ። የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር በኢትዮጵያ የነበረው ቆይታ ተደመደመ! የጎንደሩ ውጊያና ሽንፈት የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር በአፍሪካ ምድር ያካሄደው የመጨረሻው ውጊያና የተከናነበው የመጨረሻው ሽንፈት ሆኖ ተመዘገበ። ቀኛዝማች ኪዳኔ ከአልጋወራሹ ጋር ወደ ወሎ ጠቅላይ ግዛት እንዲሄዱ ተደርጎ እዚያው ብዙ ወታደርና መሳሪያ ለመከላከያ ሚኒስቴር አስረከቡ።

በየካቲት 1934 ዓ.ም የፊታውራሪነት ማእረግ አግኝተው መጀመሪያ በወረዳ አስተዳዳሪነት ከዚያም በ1936 ዓ.ም የየጁ፤ የዋድላ ደላንታ፤ የመቄት፤ የሸደሆና የዳውንት ብሔራዊ ጦር አዛዥና የጠቅላይ ግዛቱ ጦር አማካሪ በመሆን አገለገሉ። ከዚያም እስከ 1943 ዓ.ም ድረስ ደግሞ በወሎና በከፋ ውስጥ በአውራጃ አስተዳዳሪነት ተመድበው ሲያገለግሉ ቆዩ። በዚሁ ወቅት ነው የደጃዝማችነት ማዕረግ የተሰጣቸው።

ደጃዝማች ኪዳኔ ከፋ ውስጥ እንደተሾሙ ከጠቅላይ ገዢው ጋር ባለመስማማታቸው ተሸረው ንጉሠ ነገሥቱ ከስልጣን እስከወረዱበት ጊዜ ድረስ በእስራትና በግዞት እንዲቆዩ ተደርገዋል። ንጉሠ ነገሥቱ ከስልጣን ከወረዱ በኋላ ደጃዝማች ኪዳኔ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር ሊቀመንበር ሆነው ተመርጠው ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ ሀገራቸውንና ማኅበሩን ወክለው ሮም ላይ በተካሄደው የዓለም አቀፍ ጸረ ኑክሊየር መሣሪያ ስብሰባ ላይ ለመሳተፍ ሲጓዙ ሞስኮ ላይ፣ ጥቅምት 9 ቀን 1972 ዓ.ም. አረፉ። ስርዓተ ቀብራቸውም ጥቅምት 15 ቀን 1972 ዓ.ም በአዲስ አበባ መንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተፈፅሟል።

ደጃዝማች ኪዳኔ ወልደመድኅን ከአርበኛነታቸው በተጨማሪ በማኅበራዊ ኑሯቸውም ንቁ ተሳታፊ ነበሩ። በ1949 ዓ.ም በትውልድ ስፍራቸው በቡልጋ የየለጥ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያንን አሰርተዋል። በ1964 ዓ.ም «ከልደት እስከ ሞት» የተሰኘች አጭር ሃይማኖታዊና የፍልስፍና መጽሐፍ አሳትመዋል።

ክቡር ደጃዝማች ኪዳኔ ወልደመድኅን ከሀገር ውስጥ በተጨማሪ በርካታ የውጭ ሀገራት ሽልማቶችን አግኝተዋል። ከእነዚህም መካከል የዳግማዊ ምኒልክ ኒሻን ባለአምበል፣ የአርበኝነት ሜዳይ ከአራት ዘንባባ ጋር፣ የድል ኮከብ ሜዳይ፣ የቅዱስ ጊዮርጊስ የከፍተኛ ጀብዱ ሜዳይ ከአንድ ዘንባባ ጋር፣ የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ታላቅ መኮንን ከደረት ኮከብ ጋር፣ የአፍሪቃ ኮከብ ሜዳይ (ከእንግሊዝ መንግሥት)፣ የአፍሪካ የድል ሜዳይ (ከእንግሊዝ መንግሥት) እንዲሁም ሦስት ልዩ ልዩ የሶቭየት ኅብረት ኒሻኖች ይጠቀሳሉ።

# ስፖርት



## በርካታ የአፍሪካ አገራት የማጣሪያ ጨዋታዎችን በገለልተኛ ሜዳ ሊያደርጉ ይችላሉ

ቦጋለ አበበ

የ2023 የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ የመጀመሪያ ጨዋታዎች ከአንድ ወር ባነሰ ጊዜ ውስጥ ይከናወናሉ። በዚህ ጊዜ ውስጥ የአፍሪካ ዋንጫው አዘጋጅ አገር ኮትዲቯርን ጨምሮ አስራ አራት አገራት የመጀመሪያ ጨዋታቸውን በገለልተኛ ሜዳ ሊያደርጉ እንደሚችሉ ሰሞኑን ከካፍ የወጡ መረጃዎች አመልክተዋል።

ኢትዮጵያ አለም አቀፍ ጨዋታዎችን በሜዳዋ እንዳታከናውን ከታገደች ከአንድ አመት በላይ ሆኗታል፤ በቀጣዩ የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታዎች እገዳውን ለማንሳት ካፍ ስቴድየሞቿን በሁለት የተለያዩ ጊዜዎች ከገመገመ በኋላ ውሳኔ ላይ እንደሚደርስ ታውቋል። ካፍ በስቴድየሞቹ መስፈርት ዙሪያ ግምገማውን ጨርሶ ብቁ ሆነው ካልተገኙ ኢትዮጵያ ጨዋታዎችን የምታደርግበት ገለልተኛ ሜዳ እንድታሳውቅ ያደርጋል ተብሎ ይጠበቃል።

በአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያው በምድብ አራት ከግብጽ፣ ማላዊና ጊኒ ጋር የተደለደለችው ኢትዮጵያ ከወር በኋላ የመጀመሪያውን የማጣሪያ ጨዋታ ከማላዊ አቻዋ ጋር ከሜዳዋ ውጪ ታደርጋለች። በመጪው ሰኔም ከግብጽ ጋር በሜዳዋ ትጫወታለች። ካፍም ኢትዮጵያ የመጀመሪያ ጨዋታዋን ከሜዳዋ ውጪ በማድረጓ ለጊዜውም ቢሆን ገለልተኛ ሜዳ በአስቸኳይ የመምረጥ ግዴታ ውስጥ እንዳትገባ ማድረጉ ይታመናል። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ ሁለተኛውን ጨዋታ በሜዳዋ የምታከናውን በመሆኑ ቢያንስ ከወር ባልበለጠ ጊዜ መስፈርት የሚያሟላ ስቴዲየም የማዘጋጀት ግዴታ ይኖርባታል።

ለዚህም ቀጣዩን የቤትኪንግ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ የሚያስተናግደው የባህርዳር ስቴድየም ባለፉት በርካታ ወራት በካፍ ግብረመልስ መሰረት የተደረገለት



እድሳት ተጠናቆ ብቁ ሊሆን እንደሚችል ተስፋ ተደርጓል። ኢትዮጵያ አለም አቀፍ ጨዋታዎችን እንዳታስተናግድ ከአመት በፊት በካፍ ከመታገዷ አስቀድሞ የባህርዳር ስቴድየም በብቸኝነት አለም አቀፍ ጨዋታዎች ሲካሄዱበት መቆየቱ ይታወቃል። ስቴድየሙ ጨዋታዎችን ሲያስተናግድ የነበረውም በካፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ከስር ከስር የማሻሻያ ስራዎችን እንዲያከናውን ተደርጎ ነበር። የማሻሻያ ስራዎቹ እየተከናወኑ በነበረበት ሁኔታም ካፍ በቂ ማሻሻያ አልተደረገም ብሎ በማመን ለእገዳ ዳርጎታል። በዚህም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ለኳታሩ የአለም ዋንጫ ማጣሪያ የመጨረሻ ጨዋታዎች ጋናንና ዚምቡዋቤን ከሜዳው ውጪ ለመግጠም ተገዶ እንደነበር ይታወሳል።

ኬንያ፣ ዩጋንዳና ርዋንዳም ስቴድየሞቻቸው ከተገመገሙ በኋላ ገለልተኛ ሜዳ መርጠው እንዲያሳውቁ ካፍ እድል እንደሚሰጣቸው ታውቋል። ከስቴድየሞች የካፍን መስፈርት አለሟሟላት፣ ከጸጥታና ሌሎች ችግሮች ጋር በተያያዘ በርካታ አገራት የማጣሪያ ጨዋታቸውን የሚያደርጉበትን ገለልተኛ ሜዳ ከወዲሁ እያሳወቁ ይገኛሉ። ቡርኪናፋሶ፣ ሌሴቶ፣ ናሚቢያ፣ ደቡብ ሱዳንና ቡሩንዲን የመሳሰሉ አገራት የማጣሪያ ጨዋታቸውን በሞሮኮ ለማድረግ ውሳኔ ላይ ደርሰዋል፤ ታንዛኒያን የመሳሰሉት አገራት በሜዳቸው ጨዋታዎችን ማስተናገድ ካልቻሉ ገለልተኛ ሜዳ መርጠው በቅርቡ ለካፍ ያሳውቃሉ ተብሎ ይጠበቃል።

ጋምቢያ፣ ላይቤሪያ፣ ሴራሊዮን፣ ዚምባቡዌ የማጣሪያ ጨዋታቸውን በሴኔጋል ለማድረግ ፍላጎት አሳይተዋል፤ ጊኒና ዛምቢያም ሴኔጋል ላይ ጨዋታቸውን የማድረግ ፍላጎት እንዳላቸውና ውሳኔ ላይ ግን እንዳልደረሱ ታውቋል።

የአፍሪካ ዋንጫውን ለማስተናገድ በዝግጅት ላይ የምትገኘው ኮትዲቯር የማጣሪያ ጨዋታዋን የምታደርግበትን ስቴድየም ለካፍ አለማስመዝገቧ አነጋጋሪ ነው። ኮትዲቯር የካፍን መመዘኛዎች የሚያሟላ ስቴድየም ከሌላቸው አገራት ተርታ ተፈርጃ የመጨረሻ አለም አቀፍ ጨዋታዋን በቤኒን ማድረጓ ይታወቃል። ይሁን እንጂ የአገሪቱ እግር ኳስ ፌዴሬሽን አዲስ እየተገነባ የሚገኘውንና ሃያ ሺ ተመልካች የሚይዘውን ያሙሱክሮ ስቴድየምን ለቀጣይ የማጣሪያ ጨዋታዎች ለመጠቀም ከካፍ ፍቃድ ጠይቋል።

የአፍሪካ ዋንጫው አዘጋጅ ኮትዲቯርን ጨምሮ የማጣሪያ ጨዋታቸውን የሚያካሂዱበት ገለልተኛ ሜዳ እንዲያሳውቁ ካፍ ጥያቄ ካቀረበላቸው አስራ አራት አገራት መካከል ማላዊ፣ ጋምቢያ፣ ሞዛምቢክ፣ ኮንጎ ብራዛቪል፣ ዚምባቡዌ፣ ሴራሊዮን፣ ጊኒ ቢሳው፣ መካከለኛው አፍሪካ ሪፐብሊክና ርዋንዳ ይገኙበታል።

ካፍ ዝቅተኛውን መስፈርት አያሟሉም ያላቸው ሃያ የአፍሪካ ስቴድየሞች ምንም አይነት አለም አቀፍ ጨዋታ እንዳያስተናግዱ ባለፈው አመት ማገዱ ይታወቃል። ካፍ በስቴድየሞቹ ላይ የጣለው እገዳ አሁንም ያልተነሳ ሲሆን አባል አገራቱም የስቴድየሞቻቸውን ደረጃ ለማሻሻል የእድሳት ስራዎችን ጨምሮ አዲስ ግንባታዎችን እያከናወኑ ይገኛሉ። ደቡብ አፍሪካ፣ ግብጽ፣ ሞሮኮ፣ ናይጀሪያና ካሜሩንን የመሳሰሉ ከአምስት ያልበለጡ አገራት ብቻ የካፍን መስፈርት የሚያሟሉ ስቴድየሞች እንዳሏቸው መረጃዎች ይጠቁማሉ።


### የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በፍ/ባለመብት እነ ወ/ሪት ትርሲት እና በፍ/ባለዕዳ እነ እናታለም ተመስገን መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር/74076፣80115 በ28/11/2012 እና በ04/12/2013 ዓ.ም እና በ10/06/2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 08 የቤት ቁጥር 392 የሆነ መኖሪያ ቤት መለያ ኮድ AA000100800210 የይዞታው ጠቅላላ ስፋት 498 ካ/ሜ ፍርድ ያረፈበት 5 (አምስት) ክፍል ቤት ስፋት 88.7 ካ/ሜ ስፋት ያለው በእነ እናታለም ተመስገን የተመዘገበ የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 354,800 (ሦስት መቶ ሃምሳ አራት ሺህ ስምንት መቶ ብር) የትራዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ሰኔ 10 ቀን 2014 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ በ4፡30 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡

የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ለመጎብኘት የሚችሉ ሲሆን፤ እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4 ኛውን በባንክ በተረጋገጠ CPO ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

- በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጉድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎችን ዳይሬክቶሬቱ የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በኢፌዴሪ ጠቅላይ ፍ/ቤት የፌዴራል ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት**

### የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

የፍ/ባለመብት ወ/ሮ አስንቃ ደሴ እና በፍ/ባለዕዳ አቶ ጌታቸው ይመር መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 98564 በ15/2/2014 ዓ.ም እና በመ/ቁ 94301 በ16/10/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 1 በጋሻ የቤት ሥራ ማህበር ውስጥ በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ጅምር ቤት ስፋቱ በካርታ 94.64 ካ/ሜ ካርታ ያለው የሊዝ እዳ 3,861,98 ያለበት የቤቱ ዲዛይን G+ 3 የሆነው የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 1,296,000 (አንድ ሚሊየን ሁለት መቶ ዘጠና ስድስት ሺ ብር ) ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ሰኔ 22 ቀን 2014 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ በ5፡30 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡

የሐራጅ ሽያጭ የሚካሄደው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ለመጎብኘት የሚችሉ ሲሆን፤ እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4 ኛውን በባንክ በተረጋገጠ CPO ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጉድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎችን ዳይሬክቶሬቱ የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬ**

### የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

የፍርድ ባለመብት ጥሩነሽ መገርሳ እና በፍ/ባለዕዳ ወ/ሮ አየሁ ገረመው መካከል ስላለው የፍርድ አፈፃፀም ጉዳይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 270096፣217105፣176518 በ16/5/2008 ዓ/ም በ28/4/2009 ዓ/ም እና በ13/5/2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 የቤት ቁጥር 1178 የሆነው ቤት ቤቱ ሰነድ አልባ ይዞታው በልኬት 316 ካ/ሜ የመንገድ ጥናት 64 ካ/ሜ የሚነካው ሲሆን የሀራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 30,545.58 (ሰላሳ ሺ አምስት መቶ አርባ አምስት ብር ከሃምሳ ስምንት ሳንቲም) ሆኖ ትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ሰኔ 7 ቀን 2014 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ በ4፡00 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል ::

የሐራጅ ሽያጭ የሚካሄደው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ለመጎበኘት የሚችሉ ሲሆን እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4 ኛውን በባንክ በተረጋገጠ CPO ማስያዝ ይኖርበታል :: ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም :: በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት ::

በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ ሐራጁ ጎድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎችን ዳይሬክቶሬት የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት**

### የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በፍ/ባለመብት እነ አቶ መለሰ ዘለቀ እና በፍ/ባለዕዳ አቶ ንጋቱ ዘለቀ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር/121474፤ 126200 በ29/10/2013 ዓ.ም እና በ11/06/2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በኮ/ቀ/ክ/ከተማ ወረዳ 8 የቤት ቁጥር 123 በካ/ቁ/ወ8/ወ7/01/641/15021/00 በእነ አበራሽ ታፈሰ ስም የተመዘገበ የቦታው ስፋት በሰነድ 329.28 ካ/ሜ የሆነ የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 774,560 (ሰባት መቶ ሰባ አራት ሺህ አምስት መቶ ስልሳ ብር) የትራዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ሰኔ 24 ቀን 2014 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ በ5፡00 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡

የሐራጅ ሽያጭ የሚካሄደው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ለመጎብኘት የሚችሉ ሲሆን ፤ እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4 ኛውን በባንክ በተረጋገጠ CPO ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጎድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎችን ዳይሬክቶሬቱ የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት**